# የቤ/ጉ/ክ/መ/ማረሚያ ቤት ኮሚሽን የሕግ ታራሚዎች እና ተከሳሾች አያያዝ ለመወሰን የወጣ ደንብ

2017 ዓ/ም

አሶሳ

**ደንብ ቁጥር ----/2017**

**በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግስት ማረሚ ቤቶች ኮሚሽን የሕግ ታራሚዎች እና ተከሳሾች አያያዝ ለመወሰን የወጣ ደንብ ቁጥር ………./2017**

የህግ ታራሚዎችና በተለያዩ ምክንያት ወደ ማረሚያ ቤቱ የሚገቡ ተከሳሾች በማረሚያ ቤት ቆይታቸው ሰብአዊ መብታቸዉና ያከበረ አያያዝ የማግኘት መብት ያለዉ በመሆኑ፤

በማረሚያ ቤት ቆይታቸዉም ታርመዉና እና በመልካም ሥነ ምግባር ታንጸዉ ህግ አክባሪ፣ ሠላም ወዳድ ዜጋ ሆነዉ ወደ ህብረተሰቡ እንዲቀላቀል ማድረግ ያለበት በመሆኑ፤

ታራሚዎችም ሆነ ሌሎች እስረኞች በማረሚያ ቤት ቆይታቸው ሊከበሩላቸዉ ስለሚገቡ መብቶችና የሚመራበት የአሠራር ሥርዓት መዘርጋት በማስፈለጉ፤

የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክላዊ መንግስት መስተዳድር ምክር ቤት በተሻሻለዉ የክልሉ ሕገ-መንግስት አንቀጽ 59 ንዑስ ቁጥር 1 በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ይህንን ደንብ አውጥቷል፡፡

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ ድንጋጌዎች

**1.አጭር ርዕስ**

ይህ ደንብ “**የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግስት የታራሚዎች እና ተከሳሾች አያያዝን ለመወሰን የወጣ ደንብ ቁጥር**........../2017 ዓ/ም ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

**2.ትርጓሜ**

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ ደንብ ውስጥ፣

1. "**አዋጅ**" ማለት የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ማረሚያ ቤት ኮሚሽንን እንደገና ለማቋቋም የወጣዉ አዋጅ ቁጥር186/2014 ማለት ነው
2. “ኮሚሽን” ማለት የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግስት ማረሚያ ቤት ኮሚሽን መቋቋሚያ አዋጅ 186/2014 ዓ/ም አንቀጽ 2 ንዑስ አንቀጽ 4 የተሰጠዉ ትርጉም ይኖረዋል ነው፤
3. “**የሴቶች ማረሚያና ማረፊያ ቤት**” ማለት በፍርድ ቤት ውሳኔ ያገኙ ሴት`ታራሚዎች የሚታረሙበት እና የመደበኛ ክስ የተመሠረተባቸው ሴት ተከሳሾች የሚቆዩበት ነው
4. “**ፍርድ ቤት**” ማለት የክልሉ ወይም የፌዴራል ፍርድ ቤት ማለት ነው፡፡
5. “**ተከሳሽ**” ማለት የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ሕዝብ ክልል መንግስት ማረሚያ ኮሚሽን ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 186/2014 አንቀጽ 2 ንዑስ አንቀጽ 14 የተሠጠው ትርጉም ይኖረዋል፡፡“
6. “**ማረሚያ ቤት**” ማለት በፍርድ ቤት ትዕዛዝ ወይም ውሣኔ መሠረት የሚላኩ ታራሚዎች ተጠብቀው የተወሰነባቸውን የእስራት ቅጣት የሚፈጽሙበት፣ የሚታረሙበትና የሚታነጹበት ተቋም ማለት ነው፡፡
7. “**ይቅርታ**” ማለት የይቅርታ አሰጣጥና አፈጻጸም ሥነ ስርዓት አዋጅ ቁጥር 134/2008 የተሰጠው ትርጉም ይኖረዋል፡፡
8. “**አመክሮ**” ማለት አንድ በሕግ ስልጣን በተሰጠው ፍርድ ቤት የእስራት ቅጣት የተፈረደበትን ታራሚ ከእስራት ዘመኑ ሁለት ሦስተኛውን እንደፈጸመ በወንጀል ሕግ እና

የተቀመጡትን ሁኔታዎች ሲያሟላ ከእስር ቤት እንዲለቀቅ የሚፈቀድበት ሁኔታ ማለት ነው፡፡

9. **"ታራሚ"** ማለት የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል መንግስት ማረሚያ ኮሚሽን ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 186/2014 አንቀጽ /2/ ንዑስ አንቀጽ 13 የተሠጠው ትርጉም ይኖረዋል፡፡

10. **"ደጋጋሚ ወንጀለኛ"** ማለት በወንጀል ሕግ አንቀጽ 67 የተጠቀሰው ትርጉም ይኖረዋል፡፡

11. **"የሕክምና ተቋም"** ማለት በኮሚሽኑ በስሩ ያሉትን ከከፍተኛ እና መለስተኛ የሕክምና ማዕከላትን ለአባላትና ለህግ ታራሚዎች የህክምና አገልግሎት የሚሰጥበት ማንኛዉም ተቋም ማለት ነዉ፡፡

12. **"ማሰቃየት"** ማለት ከተከሳሽ ወይም ታራሚ መረጃ ለማግኘት ወይም ለሌላ ማናቸውም ምክንያት የሚካሔድ አካላዊ ወይም አዕምሮዓዊ ስቃይና ጭንቅ፣ እንዲሁም ሰውየው ወይም ሌላ ሦስተኛ ወገን ለማስፈራራት ወይም በአድልዎ ላይ የተመሰረተ ማንኛውም ጭካኔ ለመፈጸም የማረሚያ ቤት ኃላፊነትን ይዞ በሚሰራ ሰው ወይም በእርሱ አነሳሽነት፣ ስምምነት ወይም አውቆ ሳለ ባለመቃወም የሚፈጸም ተግባር ሲሆን ነገር ግን ከሕጋዊ ቅጣቶች የሚመነጭ ወይም ከዚሁ ጋር መሠረታዊ ቁርኝት ያለውን ስቃይ አይጨምርም

13. "የማይድን በሽታ" ማለት አንደ ኤች አይ ቪ፣ሰኳር ህመም ፣ነርቪ በሽታ ፣የአዕምሮ በሽታ፣ጉበት እና የመሳሰሉት ማለት ነው፡፡

## 3. የደንቡ ተፈፃሚነት ወሰን

ይህ ደንብ የክልሉ ፖሊስ ኮሚሽን በሚያስተዳድራቸው ማረሚያ ቤቶች ሥር በሚገኙ የህግ ታራሚዎችና ተከሣሾች ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

## 4.የፆታ አገላለፅ ፣

በዚህ ደንብ ውስጥ በወንድ ፆታ የተደነገገው የሴትንም ፆታ ያካትታል፣

## 4.መሰረታዊ መርሆች

የህግ ታራሚዎች አያያዝ በሚከተሉት መሰረታዊ መርሆች ላይ የተመሰረተ ይሆናል

1) በማረሚያ ቤት ቆይታው ሰብአዊ መብቱን፣ ሰብአዊ ክብሩን እና ጤንነቱን ያከበረ አያያዝ የማግኘት፤

2) የህግ ታራሚ ወይም ተከሳሽ ሰብዓዊ ክብሩን ከሚያዋርድ፣ ጭካኔ ከተሞላበት እና ጤንነቱን አደጋ ላይ ከሚጥል አያያዝ የመጠበቅ

3) በዘር፣ በብሔር፣ ብሔረሰብ፣ በዜግነት፣ በቀለም፣ በጾታ፣ በቋንቋ፣ በሃይማኖት፣ በፖለቲካ ወይም ሌላ አመለካከት ወይም አቋም፣ በማህበራዊ አመጣጥ፣ በሐብት፣ በትውልድ አከባቢ፤በአካል ጉዳተኝነት ወይም ሌላ ምክንያት ልዩነት ያለማድረግ፤

4) የፍርድ ውሳኔ አፈፃፀም የህግ ታራሚዎችን በማረም እና በማነፅ፣ የባህሪ ለውጥ በማምጣት ወደ ሕብረተሰቡ ሲቀላቀሉ ዳግም ወንጀል እንዳይፈፅሙ የሚያደርግ የአሰራር ሥርዓት መዘረጋት፣

5) ተከሳሾች በወንጀል እንደ ጥፋተኛ ያለመቆጠርና የተፋጠነ የፍርድ ሂደት እንዲያገኙ የሚያስችል መሆኑ፤

## ክፍል ሁለት

## የህግ ታራሚዎች ወይም ተከሳሾች ቅበላ፣ ምዝገባና ለይቶ ስለመያዝ፣

### 4. ስለመቀበልና ስለመመዝገብ

1) ማረሚያ ቤት አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎች መሟላታቸውን በማረጋገጥ በፍርድ ቤት ትዕዛዝ የህግ ታራሚዎችና የቀጠሮ እስረኞችን ሲቀበል የሚከተሉትን መረጃ መመዝገብ ይኖርበታል፡-

ሀ) ማረሚያ ቤት መዝገብ ቁጥር

ለ) ማረሚያ ቤት የገባበት ቀን

ሐ) የእናት ሙሉ ስም

መ) ትውልድ አድራሻ

ሠ) በወንጀል ተጠርጥሮ የተያዘበት ቦታ (አድራሻ)

ረ) ከመያዙ በፊት የሚኖርበት አድራሻ፤

ሰ) በወንጀል ተጠርጥሮ ሲያዝ በምርመራ የቆየበት ፖሊስ ጣቢያ

ሸ) በአመክሮና ያለአመክሮ የሚፈታበትን ጊዜ፤

ቀ) ተመዝግቦ የተያዘ የግል ጥሬ ገንዘብና ሌላ ንብረት ብዛትና ዓይነት

በ) በዚህ ደንብ አንቀጽ ------- መሠረት የሚደረግ ሙሉ የሕክምና ምርመራ ውጤት፤

2) የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ድንጋጌ እንደተጠበቀ እስረኛው በማረሚያ ቤት በሚቆይበት ጊዜ የሚከተሉት መረጃዎች መመዝገብ አለባቸው፡-

ሀ) ጉዳት ወይም ሞት የደረሰባቸውን ሁኔታዎችና ምክንያቶች እንዲሁም የተወሰደ መፍትሔ፤

ለ) ዝርዝር የህግ የታራሚዎች/ ተከሳሾች ፍላጎት

ሐ) የመጀመሪያ ጥናት ድልደላ ሪፖርት

መ) ዝውውር ከተከናወነ የተካሔደበት ክልል፣ ዞን፣ ወረዳ ወይም ማረሚያ ቤት፣ ዓመተ ምህረት፤ወር፤ ቀንና ሰዓት እና

ሠ) ሌሎች ተያያዥነት ያላቸው መረጃዎች፤

3) ወደ ማረፊያ ቤት የሚገቡ የህግ ታራሚዎጭ ወይም የቀጠሮ እስረኞችን ኮሚሽኑ በሚያወጣው መመሪያ መሠረት የግል ማህደር እንዲኖራቸው ይደረጋል፤

4) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 መሠረት የሚደራጀው ማህደር ውስጥ የህግ ታራሚ ወይም ተከሳሹ የቅደመ አካላዊ ጉዳት መኖር አለመኖር እንዲሁም ጉዳቱን ተመልክቶ የቀረበ ቅሬታ እና ውጤት ተመዝግቦ እንዲቀመጥ ይደረጋል፤

5) ማህደሩ የህግ ታራሚውን/ተከሳሹን ማንነት የሚገልጽ የፎቶ ግራፍ፣ የድምጽና የጣት አሻራ በመቀበል ሙሉ የሕይወት ታሪኩን በመመዝገብ ስለመረጃው ትክክለኛነት ታራሚው ወይም ተከሳሹ በሚገባው ቋንቋ ተነቦለት በፊርማ ከመዝጋቢው ፖሊስ ጋር በጋራ እንዲያረጋግጡ ይደረጋል፣

6) ማንኛውም የህግ ታራሚ ወይም የቀጠሮ እስረኛ ማረሚያ በሚገባበት ዕለት ጠቅላላ የጤና ምርመራና የማረጋጋት አገልግሎት እንዲያገኝ ይደረጋል፣

7) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 እስከ 4 መሠረት የተከናወኑ ምዝገባዎች የህግ ታራሚዉና የቀጠሮ እስረኛው ጥያቄ ሲያቀርብ በነጻ ይሰጣል፤ ሆኖም ማስረጃው በነጻ የሚሰጠው ለአንድ ጊዜ ይሆናል፡፡አፈጻጸሙ በመመሪያ ይወሰናል፡፡

5. **የህግ ታራሚዎችና የቀጠሮ ተከሳሾች ለይቶ ስለመያዝ**

1. ሴት የህግ ታራሚዎችንና የቀጠሮ እስረኞችን የሚጠብቁና የሚቆጣጠሩት ፖሊስ አባሎችና ኃላፊዎች ሴቶች ብቻ ሲሆኑ ዙሪያ ጥበቃው በወንድና የሴት ማረሚያ ፖሊስ አባላት ሊከናወን ይችላል፡፡
2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ የማረሚያ ቤቱ ልዩ ልዩ የሙያ ስራዎች ሴት ወይም ወንድ የማረሚያ ፖሊስ ወይም ሲቪል ሠራተኞች ሊከናወን ይችላል፣
3. ዕድሜያቸው ከ65 ዓመት በላይ የሆኑ አዛውንት የህግ ታራሚዎችና የቀጠሮ እስረኞች ከሌሎች ተለይተው እንዲያዙ ይደረጋል፣
4. የአካል ጉዳት ያላቸው የህግ ታራሚዎች ወይም እስረኞች እንደ ጉዳታቸው መጠን ምቹ በሆነ የመኖሪያ ክፍል እና አካባቢ እንዲያዙ ይደረጋል፤
5. በፍትህ አካላት ስር ሲሰሩ የነበሩ የህግ ታራሚዎች የቀጠሮ ተከሳሾች በዞን ወይም በቤት ተለይተው እንዲያዙ ይደረጋል፤
6. ነፍሰ ጡር እና ሁለት ዓመት ያልሞላቸውን ሕፃናት የያዙ ሴት የህግ ታራሚዎችና የቀጠሮ እስረኞች በፈፀሙት ወንጀልና በፍርድ ዓይነት፤ በቤት ተለይተው እንዲያዙ ይደረጋል፤
7. በጤና ሚኒስቴር ተላላፊ ተብለው የተመደቡ በሽታዎች እንደአስገዳጅነቱ ተለይተው ይያዛሉ፣
8. የአእምሮ ሕመም ችግር ያለባቸው የህግ ታራሚዎች/ተከሳሾች እንዳስፈላጊነቱ ወይም በሐኪም ሲታዘዝ ከሌሎች ተለይተው ይያዛሉ፤
9. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) እስከ (8) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ኮሚሽኑ ለእርምት ሥራ ውጤታማነት በሚያግዝ ሁኔታ የህግ ታራሚዎችን ለይቶ መያዝ ይችላል፡፡
10. ከፍተኛ ጥበቃ የሚያስፈልጋቸው ታራሚዎች ከሌሎች የህግ ታራሚዎችና ተከሳሾች ተለይተው ይያዛሉ፣
11. እድሜያቸው ከ18 ዓመት በታች የሆኑ የህግ ታራሚዎች ወይም የቀጠሮ ተከሳሾች ከአዋቂዎች ተለይተው ይያዛሉ፣

12. ሁኔታዎች በፈቀዱ መጠን ያልተፈረደባቸው ታራሚዎች ከተፈረደባቸው የህግ ታራሚዎች ተለይተው ይያዛሉ፤

13. ሁኔታዎች በፈቀዱ መጠን ከባድ የወንጀል ሪከርድ ያለባቸው እና ደጋጋሚ የወንጀል ድርጊት የፈጸሙና ምግባረ ብልሹ የህግ ታራሚዎች ከሌሎች ታራሚዎች ተለይተው ይያዛሉ፤

## 6.የህግ ታራሚዎችና የቀጠሮ ተካሳሾች የሚኖሩባቸዉ ክፍሎች ማሟላት ስለሚኖርባቸዉ ሁኔታዎች፤

1. የህግ የታራሚ ወይም የቀጠሮ የተከሣሽ መኖሪያ ክፍሎች እና መስሪያ ቦታዎች በቂ አየርና ብርሃን የሚያስገቡና መስኮቶች ያላቸው እና በቀንም ሆነ በሌሊት የዓይን ጤንነት የማይጐዱ መብራት ያሏቸው መሆን አለባቸው፣
2. የህግ ታራሚ ወይም የቀጠሮ ተከሳሾች የምግብ አዳራሽ ንፁህናዉ የተጠበቀና ምቹ የሆነ የምግብ አዳራሽ እንዲኖር ይደረጋል፡፡
3. የህግ ታራሚዎች የቀጠሮ ተከሳሾች የሚኖሩባቸዉና በጋራ የሚገለገሉባቸዉ ግቢዎች ንጽህናቸዉ ለጤና ተስማሚ መሆን አለባቸዉ፡፡

7. **ስለ ልብስ**

1. ማንኛውም የቀጠሮ ተከሳሽ እና የህግ ታራሚ በግቢና ከግቢ ውጭ ወደ ፍርድ ቤት እና ሌሎች ቦታዎች ሲሄድ በኮሚሽኑ የተዘጋጀውን ዩኒፎርም መልበስ አለበት፣
2. ዩኒፎርሙ ንጽህናውን የጠበቀ፤ የአየር ጸባይ ከግምት ያስገባና ቅያሪ ያለውና ክብር ዝቅ የማያደርግ መሆን ይገባዋል፡፡
3. የተከሳሽ እና ፍርደኛ የህግ ታራሚዎች አልባሣት በቀለም የተለያዩ ይሆናሉ
4. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ቢኖርም በጤና ምክንያት በሐኪም ትዕዛዝ ተቋሙ ለህግ ለታራሚው ወይም የቀጠሮ ተከሳሹ ለጤናው ተስማሚ የሆነውን ልብስ እንዲለብስ ሊፈቀድ ይችላል፡፡
5. በጤና ምክንያት ሐኪም ካዘዘ ተጨማሪ የመኝታ ልብስ ለእስረኛ ሊሰጥ ይችላል፡፡

8. ስለ ጽዳት

1) የህግ ታራሚ ወይም የቀጠሮ ተከሳሽች በየጊዜው ንጽሕናቸውን የሚጠብቁበት በቂ ውሃ ማግኘት አለባቸው

2) የህግ ታራሚዎች ወይም የቀጠሮ ተከሳሽ የንጽሕና መጠበቂያ ቁሳቁስ እንዲሁም የመታጠቢያ ቦታና ለአገልግሎት ዝግጁ የሆነ የመጸዳጃ ቤት እንዲኖራቸው ይደረጋል፡፡

9. ስለ ምግብ

1) ማንኛውም ሰው በታራሚው የአዕምሮ ወይም የአካል ጤንነት ላይ ጉዳት የሚያስከትሉ ምግብ ወይም መጠጦች ማስገባት የለበትም፤

2) ማንኛውም ሰው ምንነቱ የማይታወቅ ወይም የመሻሪያ ጊዜው የደረሰ ምግብ ወይም መጠጥ ወደ ማረሚያ ቤት ማስገባት የለበትም፤

3) ማንኛውም ሰው መጠናቸው ከታራሚው ፍጆታ በላይ የሆኑ ምግቦችን ወይም መጠጦችን ወደ ማረሚያ ቤት ማስገባት የለበትም፤

4) የውጭ ዜጎች ባህላቸውን መሠረት ያደረገ ምግብ እንዲቀርላቸው ኮሚሽኑ ያመቻቻል፤

5) ማንኛዉም ታራሚ ወይም ተከሳሽ ለጤንነት የሚስማማና በቂ ምግብ በቀን ሦስት ጊዜ በማረሚያ ቤቱ ይቀርብለታል፡፡

10. ስለ መኝታ

1. ማንኛዉም የህግ ታራሚ ወይም የቀጠሮ እስረኛ አስፈላጊ የሆነዉን መኝታና የመኝታ ልብስ እንዲያገኝ ያደረጋል፤

2. በጤና ምክንያት ሀክም ከዘዘ ወይም ኮሚሽኑ ከፈቀደ ተጨማሪ የመኝታ ልብስ ለታራሚዉም ወይም ለተከሳሹ ልሰጥ ይችላል

11.ስለ ሕክምና

1. የህግ ታራሚዎች ወይም ተከሳሾች ነፃ የሕክምና አገልግሎት የማግኘት መብት አላቸው፣

2. በማረሚያ ቤት ውስጥ ለሚገኙ ለህግ ታራሚዎችና ተከሳሾች አገልግሎት የሚሰጥ የሕክምና መስጫ ጣቢያ፣ የተሟሉ የሕክምና መሳሪያዎች፣ መድሃኒቶች፣ ላብራቶሪና የሕክምና ባለሙያዎች ይኖሩታል፣

3. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) ድንጋጌ ቢኖርም፣ ማንኛውም መድሐኒት የሕክምና ባለሙያ ካልፈቀደ በስተቀር ወደ ማረሚያ ቤት እንዲገባ ወይም ታራሚዎች እና ተከሳሾች እንዲጠቀሙበት አይደረግም ፣

4. ማንኛውም የህግ ታራሚ ወይም የቀጠሮ ተከሳሽ ወደ ሌላ የህክምና ተቋም ተልኮ እንዲታከም ከሕክምና ባለሙያው በቀረበው ማስረጃ መሠረት ወደ ሌላ መንግስታዊ ወደሆነ ሕክምና ተቋም ተዛውሮ እንዲታከም ሊደረግ ይችላል፣

5. የማረሚያ ቤቱ የንጽህና ሁኔታ እና የምግብ የጥራት ደረጃ በሕክምና ኃላፊው ቁጥጥር ይደረግበታል፡፡ መስተካከል የሚገባው ካለም የሕክምና ኃላፊው እያጠና ለኮሚሽኑ ሃሳብ ያቀርባል፣ አፈፃፀሙንም ይከታተላል፣

6. የሕክምና ኃላፊው የዲስፒሊን ቅጣት የተወሰነበት ታራሚ ወይም ተከሳሽ ቅጣቱ ለጤንነቱ ጎጂ መሆኑን ካረጋገጠ ቅጣቱ እንዲቋረጥ ወይም እንዲቀየር ለማረሚያ ወይም ለማረፊያ ቤቱ ሃሳብ ያቀርባል፣

7. ነፍሰ ጡር የሆነች ሴት የህግ ታራሚ ወይም የቀጠሮ ተከሳሽ የመውለጃ ጊዜዋ ሲደርስ በቂ የሕክምና አገልግሎት ወደሚገኝበት ተቋም ተወስዳ እንድትወልድ ይደረጋል፡፡ ሆኖም ሕፃኑ በማረሚያ ቤቱ ውስጥ የተወለደ ከሆነ ይኸው ሁኔታ በልደት የምስክር ወረቀቱ ላይ አይጠቀስም፣

8. በክልሉ የመንግስት ሆስፒታል ታክሞ ሊድን ያልቻለ ታራሚ ወይም ተከሳሽ ወደ ከፍተኛ ህክምና ሄዶ እንዲታከም በዶክተር ሲታዘዝና ሪፈር ሲባል ህክምናውን እንዲያገኝ ማረሚያ ቤቱ ተገቢውን ድጋፍ ያደርጋል የህክምና ወጪውንም ይሸፍናል እንዲሁም ታካሚው በራሱ ወጪ በግል ሆስፒታል እንዲታከም ጥያቄ ሲያቀርብና ያቀረበው ጥያቄ በኮሚሽኑ ተቀባይነት ሲያገኝ የህክምና አገልግሎቱን እንዲያገኝ ሊፈቅድ ይችላል፡፡

9. ማንኛዉም የህግ ታራሚ ሌሊት ህመም ያጋጠመ እንደሆነ ክፍሉ ተከፍቶ እንድታከም ይደረጋል አፈፀፀሙ በመመሪያ ይወሰነል፡፡

## 12. ልዩ ድጋፍና እንክብካቤ ስለሚያስፈልጋቸው የህግ ታራሚዎች ወይም የቀጠሮ ተከሳሾች

1) ዕድሜያቸው ከ18 ዓመት በታች፣ አካል ጉዳተኞች፣ በዕድሜ የገፉ አዛውንቶችና በማይድን በሽታ የተያዙ፣ አዕምሮ ሕመምተኞች፣ ሞት ፍርደኞችና የዕድሜ ልክ ፍርደኞች የህግ ታራሚዎችና ተከሳሾች፤

2) በማረሚያ ቤት ያሉ ሴቶች፣ ነፍሰጡርና እመጫት ታራሚዎችና ተከሳሾች እና

3) ከእናቶቻቸው ጋር በማረሚያ ቤት የሚገኑ ሕጻናትና ሌሎች፣ ልዩ ድጋፍና እንክብካቤ ይደረግላቸዋል፡፡ ዝርዝሩ በመመሪያ ይወሰናል፡፡

## 13. ስለ ነፍሰጡር ሴት የህግ ታራሚ እና እመጫትና ሕጻናት፣

1. 1 ሴት የህግ ታራሚ ወይም ተከሳሽ ዕድሜው ሁለት ዓመት ያልሞላው ሕፃን ይዛ ከመጣችና ለልጁ አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ ሕፃኑ በማረሚያ ቤቱ ውስጥ ከእናቱ ጋር እንዲቆይ ይደረጋል፣

2. ሕፃኑ በማረሚያ ቤት ቆይታው አስፈላጊውን ምግብ፣ ክትባት፣ ሕክምና እንዲሁም ለሕጻኑ አስፈላጊ የሆነ መኝታና የመኝታ ልብስ እንዲያገኝ ይደረጋል፣

3. ሕፃኑ በማረሚያ ቤት በመቆየቱ በአካሉ ወይም በሥነ ልቦናው ችግር የሚያመጣበት ሆኖ ሲገኝ ለቅርብ ዘመድ እንዲሰጥ ይደረጋል፡፡ሆኖም የቅርብ ዘመድ የማይገኝ ከሆነ ሕፃኑ ሌላ አሳዳጊ የሚያገኝበትን ሁኔታ ተቋሙ ያመቻቻል፣

4. ነፍሰ ጡር ሴት የህግ ታራሚ ወይም እመጫት የሆነች የህግ ታራሚ ወይም ተከሳሽ በሐኪም ትዕዛዝ ተጨማሪ ምግብ እንድታገኝ ይደረጋል፡፡

5. ከላይ በንዑስ አንቀጽ 3 የተቀመጠው ዘመድ የማይገኝ ከሆነ ሕፃኑ ሌላ አሳዳጊ የሚያገኝበትን ሁኔታ ተቋሙ ያመቻቻል፣

## 14. ከጐብኝዎች ጋር ስለሚደረግ ግንኙነት

1 ማንኛውም የህግ ታራሚ ወይም የቀጠሮ ተከሳሽ ከማረሚያ ወይም ማረፊያ ቤት ውጪ በእጀባ ወቅት ሊጎበኝ አይችልም፣ ሆኖም በሆስፒታል ተኝቶ በመታከም ላይ የሚገኝ እስረኛ የጉብኝት ሁኔታ በመመሪያ ይወሰናል፣

2) ጉብኝቱ ለማረም ማነጽ እና ለጥበቃና ደህንነት ስራዎች በሚያመች ሁኔታ ይከናወናል፣

3) የህግ ታራሚ ወይም የቀጠሮ ተከሳሽ በመደበኛ ጉብኝት ቦታ እንዲጐበኙ ለማድረግ አመቺ ባልሆነ ጊዜ የማረሚያ ቤቱ ኃላፊ ሲፈቅድ በአንድ ቦታ በሕብረት እንዲጐበኙ ሊደረግ ይችላል፡፡

4) አካል ጉዳተኛ፣ የአዕምሮ ህሙማን ወይም በጽኑ በሽታ በአልጋ ላይ የሚገኙና አራስ የህግ ታራሚ እና የቀጠሮ ተከሳሽ ምቹ በሆነ ቦታ ጉብኝቱ ይከናወናል፣

5) ጎብኚው አካል ጉዳተኛ እና አቅመ ደካማ ከሆነ ኮሚሽኑ የጉዳቱን መጠን አይቶ ምቹ በሆነ ቦታ ጉብኝቱ እንዲከናወን ያደርጋል

6) ማንኛውም ሰው ጎብኝት ሲያከናውን በተቋሙ የጉብኝት መመሪያ ላይ የተደነገጉትን መስፈርቶች ማሟላት አለበት

7) የውጭ ዜጋ የህግ ታራሚ የቀጠሮ እስረኛ በአገሩ ኤምባሲ ወይም ቆንሲላ እንዲሁም ማንኛውም ሰው እንዲጐበኝ ይፈቀድለታል፡፡ዝርዝር አፈጻጸም በመመሪያ ይወሰናል

8). የህግ ታራሚዎች ወይም ተከሳሾች ከትዳር አጋሮቻቸው፣ ከቅርብ ዘመዶቻቸው፣ ከጓደኞቻቸው፣ ከሐኪሞቻቸው፣ ከሕግ አማካሪዎቻቸው፣ ከሃይማኖት አባቶቻቸውና መሪዎቻቸው ጋር የመገናኘት መብት አላቸው፣

## 15. ጎብኝዎችን ስለመፈተሽ

1) ማንኛውም ጎብኝ የታደሰ መታወቂያ፣ ፓስፖርት፣ መንጃ ፈቃድ ወይም ማንነቱንና የመኖሪያ አድራሻውን የሚገልጽ ማስረጃ በማሳየት በተመሳሳይ ፆታ የማረሚያ ፖሊስ ተፈትሾ እንዲጐበኝ ይደረጋል፣

2) ማንኛውም ጎብኝ ማንነቱን በግልጽ እንዲያሳይ ተጠይቆ ፈቃደኛ ካልሆነ ታራሚን ወይም ተከሳሽን እንዲጐበኝ አይፈቀድለትም፣

3) ማንኛውም ጎብኝ እንዲፈተሽ ተጠይቆ ፈቃደኛ ካልሆነ እስረኛንእንዲጐበኝ አይፈቀድለትም፣

4) ማንኛውም ጎብኝ የህግ ታራሚ ወይም የቀጠሮ እስረኛን ጎብኝቶ ሲወጣ መፈተሽ ይኖርበታል፡፡

## 16. ጎብኝዎችንና የህግ ታራሚዎችን ወይም ተከሳሾችን ስለ መቆጣጠር

1) የህግ ታራሚ ወይም የቀጠሮ ተከሳሽ ከጎብኝዎቻቸው ጋር በሚነጋገሩበት ጊዜ ለጥበቃ ሥራ ተቃራኒ የሆነ ተግባር እንዳይፈጸም ጉብኝቱን በማያስተጓጉል አግባብ ቁጥጥርና ክትትል ይደረጋል፣

2) ማንኛውም የቀጠሮ እስረኛ ከሕግ አማካሪው ወይም ከጠበቃው ጋር ግንኙነት ሲያደርግ በማረሚያ ፖሊስ አባላት እይታ ሥር ሆኖ ንግግሩን በማያዳምጡበት ሁኔታ ይካሄዳል፡፡

3) ማንኛውም ጎብኚ የህግ ታራሚ ወይም ተከሳሾችን ለመጎብኘት ሲመጣ ማንነቱን የሚገልጽ በመንግስት የተሰጠ የታደሰ መታወቂያ ወይም ፓስፖርት ወይም መንጃ ፈቃድ የማሳየት እና የመመዝገብ ግዴታ አለበት፤

4) በኢፌድሪ የወንጀል ሕግ በግልጽ ወንጀል ተደርገው ያልተደነገጉ እንደ ሲጋራ፣ ጫት፣ ሺሻ፣ ቡሪ፣ አንጋዳና በሐኪም ያልተፈቀዱ መድሐኒቶች፣ አልኮል፣ ስለት፣ ቤንዚንና ተቀጣጣይ የመሰሉ ነገሮችና የመገናኛ መሣሪያዎችና ለማረሚያ ቤቱና በታራሚው ላይ ደህንነት አደጋ ውስጥ የሚከቱ ኤሌክትሮኒክስ ይዞ የመጣ ጎብኝ ይህንን ለማረሚያ ፖሊስ ማሳወቅ እየተገባው ያላደረገ አግባብነት ባለው በወንጀል ሕግ በተመለከተው የደንብ መተላለፍ ሕጎች ተጠያቂ ይደረጋል፤

## 17. ቤተሰቦቻቸውን ስለሚጠይቁ ሕፃናት

1) ዕድሜው ከዘጠኝ አመት በታች የሆነ ማንኛውም ሕፃን ከአዋቂ ሰው ጋር ካልሆነ በስተቀር ብቻውን እስረኛን እንዲጠይቅ አይፈቀድለትም፣

2) ዕድሜያቸው ከ 9 እ ስከ 18 ዓመት የሞላቸው የትምህርት ቤት ወይም ማንኛውም ዓይነት ማንነታቸውን የሚያረጋግጥ ሠነድ በመያዝ ለብቻቸው ሊጠይቁ ይችላሉ፤

## 18. ከውጭ አለም ጋር ስለሚደረግ ግንኙነት

1. ማንኛውም የህግ ታራሚ ወይም የቀጠሮ ተከሳሽ ከትዳር አጋሮቻቸው፣ ከቅርብ ዘመዶቻቸው፣ ከጓደኞቻቸው፣ ከሐይማኖት አማካሪዎቻቸው፣ ከሐኪሞቻቸው እና ከሕግ አማካሪዎቻቸው ጋር የመገናኘት መብት አላቸው፣

2. የህግ ለታራሚዎችና የቀጠሮ ተከሳሾች ደህንነት፣ የማረሚያ ቤቱ ደንብና ሥርዓት ለማስከበር የሚተገብራቸው ምክንያታዊ የቁጥጥር ሥርዓቶች እንደተጠበቁ ሆነው ታራሚዎች ወይም ተከሳሾች ከማረሚያ ውጭ ካሉ ሰዎች ጋር በጽሁፍ፣ በስልክ፣ ሚዲያ እና ህትመቶች እንዲያገኙ ይፈቀድላቸዋል፡፡

3. የፕሬስ ውጤቶቹ ወቅታዊ የሆኑ መንግስታዊ ጋዜጦችና ተቋማዊ ሕትመቶች ሆነው እነዚህም በንባብ፣ በመቅረፀ ድምጽና ምስል የተዘጋጁ ሊሆኑ ይችላሉ፡

4. በማረሚያ ቤት ቆይታው በሚዲያ ተቋማት የመጎብኘት እና ቃለ ምልልስ የመስጠት መብት አለው

19. **ዝውውር**

1) ማንኛውም የህግ ታራሚ ከቤኒሻንጉል ጉሙዝ ማረሚያ ቤት ወደ ሌላ ክልል ማረሚያ ቤት ወይም ከክልል ማረሚያ ቤቶች ወደ ፌዴራል ማረሚያ ቤቶች እና በክልሉ ማረሚያ ቤቶች ኮሚሽን ከአንድ ዞን ወደ ሌላ ዞን ማረሚያ ቤት መዛወር ይችላል፡፡
2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀፅ 1 መሰረት ዝውውር የሚደረገው የህግ ታራሚው በሚያቀርበው የግል ጥያቄ ወይም በኮሚሽኑ ይሆናል፤
3) ማንኛውም የህግ ታራሚ ከክልል ማረሚያ ቤቶች ወደ ሌላ ክልል ማረሚያ ቤት ወይም ከአንዱ ዞን ወደ ሌላ ዞን ማረሚያ ቤት መዛወር የሚችለው የይግባኝ ጉዳዩ ውሳኔ ሲያገኝ እና የገንዘብ ቅጣት ያለበት ከሆነ ቅጣቱን መክፈሉ ሲረጋገጥ ወይም በፍርድ ቤት ቅጣቱን መቀየሩ ወይም መቅረቱ ሲረጋገጥ ይፈጸማል፤
4) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀፅ 2 መሰረት በግል የሚቀርብ የዝውውር ጥያቄ ተፈፃሚ የሚሆነው እስረኛው ለመዛወር የጠየቀበት ክልል ወይም ወረዳ ወይም ዞን ማረሚያ ቤት እስረኛውን ተቀብሎ ቀሪ የእስር ጊዜውን ለማስፈፀም የሚችል ስለመሆኑ ስምምነቱን ሲገልጽ ይሆናል፣
5) በግል ጥያቄ የሚደረግ ዝውውር ወጪውን የሚሸፍነው የመንግስት አሰራር በሚፈቅደው የአበል እና ትራንስፖርት ክፍያ መሰረት በሚዛወረው ታራሚ ነው፤
6) በግል ጥያቄ የሚደረግ ዝውውር የሚፈቀደው ለአንድ ጊዜ ብቻ ይሆናል፣
7) በግል ከሚከናወኑ ዝውውር ውጭ ያሉ ዝውውሮች የታራሚውን ዕድሜን፣ ፍላጎትን፣ ጤንነት ሁኔታን፣ የእስር ቆይታን፣ ግላዊ ባህሪ ደረጃ፣ የወንጀል ዓይነት ፣ የፍርድ መጠን እና ተጋላጭነት ወይም ሌላ ምክንያታዊ መስፈርት መሠረት በማድረግ ዝውውር ያደርጋል፤ ዝርዝሩ በመመሪያ ይወሰናል፡፡

20. **ስለ ፖሊስ ቃል መቀበልና የፍርድ ቤት መጥሪያ ስለመስጠት፣**

1) የፍርድ ቤት ትዕዛዝ የያዘ ፖሊስ ወደ ማረሚያ ቤት በመግባት ታራሚ ወይም እስረኛን ቃል መቀበል ይችላል፣

2) በሌላ ወንጀል የሚፈለግ የህግ ታራሚና የጊዜ ቀጠሮ እስረኛ ቃል ለመቀበል የሚቻለው ለዚህ ተለይቶ በተዘጋጀና ለዕይታ ግልጽ በሆነ ቦታ ቃል የመቀበል ሒደቱን በማያስተጓጉል አግባብ ይሆናል፤

3) የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ምርመራው በተወሰነ ጊዜና ድግግሞሽ ምክንያታዊ ቆይታ የሚወስድ መሆን አለበት፡፡

4) በዚህ አንቀጽ መሠረት ምርመራ ለማድረግ ወደ ማረፊያ ቤት የሚመጣ መርማሪ ማንነት ተመዝግቦ እንዲያዝ ይደረጋል፡፡

5) ማንኛውም ሰው የማረሚያ ቤት ኃላፊ ሲፈቅድ በመደበኛ ሥራ ሰዓት ወደ ማረሚያ ቤት በመግባት ለእስረኛ የፍርድ ቤት መጥሪያ መስጠት ይችላል፡፡

21. የህግ ታራሚ ሞት ስለማሳወቅ፤

አንድ ማረሚያ ቤት በሞት የተለየ ታራሚ ወይም ተከሳሽ ሲኖር፣

1) የአሟሟቱን ሁኔታ ፖሊስ ምርመራ እንዲደረግ ያደርጋል፤

2) የአስከሬን ምርመራ በሆስፒታል በማድረግ ማስረጃውን ሥልጣን ላለው ፍርድ ቤት ያሳውቃል፣ መረጃውም ተደራጅቶ በኮሚሽኑ እንዲያዝ ይደረጋል፣

3) የህግ ታራሚው ወይም የተከሳሹ መሞቱን ለቤተሰቡ ወይም ለዘመዱ ያሳውቃል፣ አስከሬኑንም የሟችን የዝምድና አይነት ማስረጃ ይዞ ለመጣ ቤተሰቡ ወይም ዘመዱ በማስፈረም ይሰጣል፡፡

4) የሟቹን አስከሬን የሚወስድ ቤተሰብ ወይም ዘመድ ካልተገኘ ማረሚያ ቤቱና ማዘጋጃ ቤት እንደእምነቱ ሥርዓት ቀብሩ ይከናወናል፤ ይህም ተመዝግቦ በመረጃነት ይያዛል፡፡

22. ስለ ኑዛዜ

ማንኛውም የህግ ታራሚ ወይም ተከሳሽ ኑዛዜ ለማድረግ ሲጠይቅ ማረሚያ ወይም ማረፊያ ቤቱ አስፈላጊው ሁኔታ እንዲመቻችለት ያደርጋል፡፡ የኑዛዜውም ሠነድ በግል ማህደሩ እና በወሳኝ ኩነቶች እንዲቀመጥ ይደረጋል፡፡

## ክፍል ሦስት

## ስለ ማረም እና ተሐድሶ አገልግሎት

23. ስለ እርምት ፍላጎት መረጃ

1) ቅበላ በሚከናወንበት ጊዜ የህግ ታራሚዎች/ተከሳሾች ከሌሎች ጋር ሳይቀላቀሉ በፊት የታራሚው ወይም የተከሳሹ ዝርዝር የእርምት ፍላጎት መረጃ ተደራጅቶ ይያዛል፡፡

2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የሚሰበሰብ መረጃ የህግ ታራሚው/ተከሳሹ ስላለው የጤንነት ሁኔታ የትምህርት ዝግጅት፣ ሥነ-ልቦናዊና አዕምሮአዊ ሁኔታ፣ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ ሁኔታዎቻቸውና ልዩ ፍላጎት እንዲሁም የሥራ፣ ሙያ እና ሌሎች ክህሎቶች መረጃ የሚያካትት ይሆናል፤

3) በዚህ አንቀጽ መሠረት የተደራጀው መረጃ መነሻ በማድረግ የመጀመሪያ ጥናት ድልደላ ሪፖርት በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ በማዘጋጀት ለቀጣይ የእርምት ዕቅድና ተግባር እንዲውል ይደረጋል፡፡

24. ስለ ትምህርትና ሥልጠና

1) የህግ ታራሚዎች የቀለም ትምህርትና ልዩ ልዩ የሙያ ሥልጠና እንዲከታተሉ ይደረጋል፣

2) ማንበብና መጻፍ የማይችሉ ታራሚዎች በኮሚሽኑ በግዴታ ትምህርት እንዲማሩ ይደረጋል፤

3) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) ያለው ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ወጣት ጥፋተኞች በትምህርትና በልዩ ልዩ ሥልጠና መስኮች እንዲሳተፉ ይገደዳሉ፡፡

4) የትምህርትና ሥልጠና አሰጣጡ በመንግስት ሥርዓተ ትምህርት መሠረት ይሆናል፣

5) ማንኛውንም የህግ ታራሚ ለወሰደው ትምህርት ወይም ስልጠና ማስረጃ በሚመለከተው የመንግስት አካል ይሰጣዋል፡፡

6) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (5) ያለው ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ የከፍተኛ ትምህርት ሊያስገባ የሚችል ውጤት ያመጡ የህግ ታራሚዎች በርቀት እንዲከታተሉ ያመቻቻል፣

7) ሴቶችና ወጣት የህግ ታራሚዎች የትምህርት እና ስልጠና ዕድል እንዲያገኙ ልዩ ትኩረት ይደረጋል፣

8) የህግ ታራሚዎች እና ተከሳሾች በማረሚያ ቤት ቆይታቸው ዕውቀትና ክህሎታቸውን ለማዳበርና የተለያዩ መረጃዎችን ለማግኘት የሚያስችሉ የቤተመፃህፍት አገልግሎት እንዲያገኙ ይደረጋል፡፡

9) ከእናቶቻቸው ጋር ወደ ማረሚያ ቤት የገቡ ሕፃናት የማቆያና መዝናኛ ቦታ እንዲሁም ለትምህርት ሲደርሱ መዋዕለ ሕፃናት እንዲኖራቸው ይደረጋል፡፡

## 25. የቤተ መፃህፍት አገልግሎት

1) የቤተ-መጻህፍ አገልግሎት የህግ ታራሚ ወይም ተከሳሽ ቁጥጥርና ደህንነት ሲባል የተቀመጡ መስፈርቶችን እንደተጠበቀ ሆነው ከክፍያ ነጻና በማናቸውም መደበኛ ሥራ ሠዓትና ቅዳሜና እሁድን ጨምሮ ለተጠቃሚ ክፍት እንዲሆኑ ይደረጋል፤
2) የማረሚያ ቤተ-መጻህፌትት በበቂ ባለሙያ የተደራጀና በውስጡ የሚገኙ መጽሃፍቶች በመጠን፣ በዓይነትና በቁጥር ለማረም ማነጽ የሚያግዙ መሆናቸውን ኮሚሽኑ ቁጥጥር ያደርጋል፤
3) የህግ ታራሚዎችና የቀጠሮ እስረኞች የንባብ ባህል እንዲያዳብሩ መደረግ አለበት፤ ላሳዩትም ለውጥ ተገቢው ማበረታቻ ያገኛሉ፡፡

## 26. ስለ ስፖርታዊና አካላዊ እንቅስቃሴና መዝናኛ

1) 1) ማንኛውም ማረሚያ ቤት የህግ ታራሚዎች ወይም ተከሳሾች ለጤንነታቸው አስፈላጊና ተስማሚ የሆነ የሰውነት እንቅስቃሴ በግልና በጋራ ማከናወን ይችላሉ፣
2) ማረሚያ ቤቱ የህግ ታራሚዎች ወይም ተከሳሾች በተለያዩ የተሃድሶና የመዝናኛ እንቅስቃሴዎች እንዲሳተፉ ለማስቻል የሚያስፈልገውን ያሟላል፤
3) የህግ ታራሚዎችና ተከሳሾች የቤት ውስጥና ከቤት ውጪ ስፖርታዊ መዝናኛዎች በነጻ እንዲያገኙ ይደረጋል
4) የህግ ታራሚዎችና ተከሳሾች ስፖርታዊ ባልሆኑ የሥነ-ጽሁፍ፣ የድራማ፣ የሙዚቃና ሌሎች ተመሳሳይነት ያላቸው ክበባት ውስጥ መሳተፍ ይችላሉ፤
5) የህግ ታራሚዎችና የቀጠሮ ተከሳሾች እርስ በርስ፣ ከኮሚሽኑ የማረሚያ ፖሊስ አባላትና ከውጪው ሕብረተሰብ ጋር አመቺ የሆነ የስፖርት ውድድር በማድረግ ወንድማማችነትና መተሣሠብ እንዲፈጠር ይደረጋል፣
6) የህግ ታራሚ ወይም የቀተሮ ተከሳሽ ስፖርታዊ ባልሆኑ የሥነ - ጥበብ እና ሥነ-ጽሁፍ፣ የድራማ፣ የሙዚቃ፣ ሚኒ-ሚዲያ መዝናኛዎችና ሌሎች ተመሳሳይነት ያላቸው ክበባት ውስጥ መሳተፍና የቴሌቪዥን እና የሬድዮ ፕሮግራም መከታተል ይችላሉ፤

## 27. ስለ ማኅበራዊ አገልግሎት

1) የህግ ታራሚዎችና እስረኞችወደ ማረሚያ ቤት ሲገቡ የማረጋጋት አገልግሎት እንዲያገኙ በማድረግ በቆይታቸው ለማረም ማነጽ ዝግጁ እንዲሆኑ ይደረጋል ፤

2) የህግ ታራሚዎችና እስረኞች በማረሚያና ማረፊያ ቤት ቆይታቸው የማኅበራዊ አኗኗር እና የሕይወት ክህሎት እንዲያዳብሩ እና መልካም ባህሪና ሥነ-ምግባር ኖሯቸው ማህበራዊ ተሳትፏቸው የተሻለ እንዲሆን ይደረጋል፤

3) የህግ ታረሚዎችና እስረኞች በማረሚያና ማረፊያ ቤት ቆይታቸው ማህበራዊ ችግሮቻቸው መፍታት የሚችሉበት የአቅም ግንባታ ስልጠና ያገኛሉ፤

## 28. ስለ ምክክር አገልግሎት

1) የህግ ታራሚዉ ወይም የቀጠሮ እስረኞች ወደ ማረሚያና ማረፊያ ቤት ከገቡበት ጊዜ ጀምሮ በተለያ የሥነ-ልቦና ችግሮች እንዳይጋለጡ የቅድመ መከላከል አገልግሎት እንዲያገኙ ይደረጋል፤

2) የህግ ታራሚዉ ወይም የቀጠሮ እስረኞች በማረሚያና ማረፊያ ቤት ቆይታቸው ጤናማ የስብዕና ዕድገት፣ የተስተካከለ አመለካከትና ባህሪ እንዲኖራቸው ምክክር አገልግሎት ይሰጣል፡፡

## 29. ስለ ንቃተ ሕግ፣ ስነ-ዜጋ፣ ስነ-ምግባር ትምህርት እና ነጻ ሕግ ድጋፍ አገልግሎት

1. የህግ ታራሚዎች በማረሚያ ቤት ቆይታቸው የሕግ ግንዛቤ እንዲኖራቸው እና በሰሩት ወንጀል ተፀፅተው ጥሩ ስነ-ምግባርን በመላበስ ሕግ አክባሪና ሠላማዊ እንዲሆኑ የሚያስችል በባለሙያ የታገዘ የንቃተ ሕግ፣ ስነ ዜጋ እና ስነምግባር ትምህርት አገልግሎት እንዲያገኙ ይደረጋል፣

2. ማረሚያ ቤቱ አቅም ለሌላቸውና ልዩ ድጋፍ ለሚሹ ተከሳሾች እና ለህግ ታራሚዎች ነጻ የሕግ ድጋፍ እንዲያገኙ ሁኔታዎችን ያመቻቻል፤

3. ከላይ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 የተደነገገው ቢኖርም ሴቶች፣ ወጣቶች፣ አካል ጉዳተኛ፣ የሞት ፍርደኞች፣ ዕድሜ ልክና የከባድ ፍርደኞች ቅድሚያ የሕግ ድጋፍ እንዲያገኙ ይደረጋ፡፡

4. የነጻ ሕግ ድጋፉ በቃል የሚሠጥ የሕግ ምክር፣ የሰነድ ዝግጅት ወይም ሌሎች ለታራሚው ፍትህ ማግኘት የሚያስችሉ አገልግሎቶችን ይጨምራል፤

5. ኮሚሽኑ ድጋፉን ለማድረግ ሕጋዊ ዕውቅና ካላቸው መንግስታዊና መንግስታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች ጋር በጋራ ይሰራል፤

30. ስለ መልሶ ማቋቋም

1. የህግ ታራሚዎች በማረሚያ ቤት ቆይታቸው በማህበር በማደራጀትና በልማት ስራዎች በማሳተፍ የሥራ ባለቤት በማድረግ ምርታማ ዜጎች እንዲሆኑ ይደረጋል፤

2. የህግ ታራሚዎች በቂ እርምት አግኝተው ከማረሚያ ቤት በሚወጡበት ጊዜ ከሕብረተሰቡ ጋር በሠላም ለመኖርና በስራ ላይ መሰማራት እንዲችሉ ለማድረግ ማረሚያ ቤቱ መንግስታዊና መንግስታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች ጋር በመተባበር የመልሶ ማቋቋም ስራዎችን ያመቻቻል፡፡

31. ስራ ስለማሰራት

1. ማንኛውም የህግ ታራሚ በማረሚያ ቤት የቆይታ ጊዜው የተሰጠውን ስራ የመስራት ግዴታ አለበት፤ ለሚሰራውም ሥራም ክፍያ ያገኛል፤ አፈጻጸሙም በመመሪያ ይወሰናል
2. የህግ ታራሚዎች በማረሚያ ቤት ቆይታቸው ሙያቸውን እንዲያጎለብቱ በተለያዩ የግብርና፣ የዕደ-ጥበባትና ልዩ ልዩ ስራዎች እንዲሰሩ ይደረጋል፤ አፈጻጸሙ በመመሪያ ይወሰናል
3. **የህግ** ታራሚዎች በሥራ ላይ ተሰማርተው የሚያገኙትን ገንዘብ እንዲቆጥቡ፤ የቁጠባ ባሕልን እንዲያዳብሩ ስልጠናና ድጋፍ ይደረግላቸዋል፡፡
4. የህግ ታራሚዎች በማረሚያ ቤት ቆይታቸው ሙያቸውንና ክህሎታቸውን እንዲያጎለብቱ ግብርና፣ አነስተኛ ኢንዱስትሪ፣ በማኅበራት ተደራጅተውና እና ሌሎች በገቢ ማስገኛ ስራዎች እንዲሰሩ ይደረጋል፤ .

32. ስለ ሥራ አመዳደብ

1) የህግ ታራሚዎች እንደ የሥራ ችሎታቸው፣ ሙያቸውና ጠባያቸው፣ ፍርዳቸው እና በእስር የቆይታ ጊዜያቸው እየታየ የሥራ ደረጃ ወጥቶላቸው እንዲሠሩ ይደረጋል፣ ፡፡
2) የህግ ታራሚው በቂ ችሎታ የሌለው ከሆነ ልምምድ እንዲያደርግና አስፈላጊ ትምህርት ስልጠና እንዲሠጠው ይደረጋል፡፡

33. በስራ ላይ ስለማይሰማሩ የህግ ታራሚዎች እና ተከሳሾች

1) በዚህ መመሪያ አንቀጽ 31 ንዑስ አንቀጽ 1 እና የዚህ ደንብ አንቀፅ 32 ድንጋጌ ቢኖርም፣

ሀ. ሴት የህግ ታራሚዎች ከእርግዝናቸው ከ6 ወር ጀምሮ እንዲሁም ከወለዱ በኋላ እስከ አንድ አመት ድረስ፣

ለ. ዕድሜያቸው ከ65 አመት በላይ የሆኑ ወንድ የህግ ታራሚዎችና ከ55 ዓ መት በላይ የሆኑ ሴት የህግ ታራሚዎች፣ እና

ሐ. በቀጠሮ ላይ ያሉ ተከሳሾች

መ . የሞት ፍርድ የተፈረደባቸው የህግ ታራሚዎች እንዲሠሩ አይገደዱም፡፡

2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ከሀ እስከ መ የተጠቀሱት የህግ ታራሚዎችና ተከሳሾች ለመሥራት እንደማይገደዱ ተገልጾላቸው ለመሥራት ከጠየቁ ሥራው ጤንነታቸውን የሚጐዳ ካልሆነ በስተቀር ለመስራት አይከለከሉም፡፡

## 34. መሟላት ስለሚገባቸው ሁኔታዎች

1) የህግ ታራሚዎች ለሥራ የሚሠማሩት፣

ሀ/ የሥራው ሁኔታ ለጥበቃ አመቺ መሆኑ ሲታመን እና

ለ/ የጤና ሁኔታቻው አስተማማኝ መሆኑን የህክምና ሀላፊው ሲያረጋግጥ ይሆናል፡፡

2) ማንኛውም የህግ ታራሚ ጎጂ በሆነና ጭካኔ በተሞላበት አኳኋን እንዲሁም በቀን ከ6 ሰዓትና በሣምንት ከ6 ቀናት የበለጠ እንዲሠራ አይደረግም፡፡

## 35. ያለ ክፍያ ስለሚሠራ ሥራ

1) የህግ ታራሚዎች በግልና በጋራ የሚገለገሉበትን ማንኛውንም ሥራ ያለክፍያ የመስራት ግዴታ አለባቸው፣

2) የህግ ታራሚዎች ወይም የቀጠሮ እስረኛ በግልና በቡድን ለጋራ ጥቅምና ማህበራዊ አገልግሎት ያለክፍያ የሚሰሩትን ሥራ አስተዳደሩ ያበረታታል፤ ድጋፍ ይሰጣል፡፡

## 36. ከማረሚያ ቤት ውጭ ስለመሥራት

1) የህግ ታራሚዎች ከማረሚያ ቤት ይዞታ ውጪ ወጥተው እንዲሰሩ አይፈቀድላቸውም፡፡

2) የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ ቢኖርም የመፈቻ ጊዜያቸው የተቃረቡ የህግ ታራሚዎች ማረሚያ ቤቱ ለህግ ታራሚን መልሶ ወደ ኅብረተሰብን የመቀላቀል ተልዕኮ እንደሚያሳክ ሲታመን ከማረሚያ ቤት ውጭ በእጀባ ወጥቶ እንዲሠራ ሊፈቀድ ይችላል፡፡

3) ከማረሚያ ቤት ውጭ ለሚሰራ የህግ ታራሚ የሚፈጸም ክፍያ በአካባቢው የገበያ ዋጋ ላይ ተመስርቶና ማረሚያ ቤቱ ከአሰሪው ጋር በሚያደርገው ስምምነት መሠረት ይፈጸማል፣

4) የህግ ታራሚዎች ከማረሚያ ቤት ይዞታና ግቢ ውጪ በመሥራት ከሚያገኙት ገቢ ላይ ለማረሚያ ቤቱ የሚፈጽሙት የመዋጮ ሁኔታ በመመሪያ ይወሰናል፡፡

## 37. አነስተኛ ኢንዱስትሪ ስለማቋቋም

1. የህግ ታራሚዎች በማረሚያ ቤት ቆይታቸው በሚያገኙት ትምህርትና ሥልጠና በቂ ንደፈ-ሐሳብ እውቀትና ክህሎት አዳብረው የሥራ ባህልና አምራች ዜጋ ሆነው እንዲወጡ ለማድረግ የሚያስችሉ አነስተኛ ኢንዱስትሪዎች እንድቋቋሙ ሁኔታዎችን ያመቻቻል ፤
2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ኢንዱስትሪዎቹ በቀጥታ ከታራሚዎች ተጠቃሚነትና የእርምት ውጤታማነት ጋር ግንኙነት ያላቸው ይሆናሉ፤
3. ማረሚያ ቤቱ ውጤታማነትና ምርታማነት ለማረጋገጥ ሲባል በህግ ታራሚዎች ላይ የጉልበት ብዝበዛ የማይፈጥር መሆኑን የማረጋገጥ ግዴታ አለበት

## 38. ስለ ሐይማኖትና እምነት ነፃነት

1. የአንድ የህግ ታራሚ ወይም የቀጠሮ እስረኛ ሐይማኖት ወደ ማረሚያ ወይም ማረፊያ ቤት ሲገባ ያስመዘገበው ሐይማኖት ይሆናል፡፡ ሆኖም በማረሚያ ወይም በማረፊያ ቤቱ ቆይታ ጊዜው ሐይማኖቱን ከቀየረ ይህን ማስመዝገብ ይችላል፣
2. ማንኛውም ህግ ታራሚ የቀጠሮ እስረኛ መንፈሳዊ መጻሕፍቶችን፣ መጽሔቶችንና ጽሁፎችን የማግኘትና የማንበብ መብት አለው፣
3. ማንኛውም ህግ ታራሚ የቀጠሮ እስረኛ የሐይማኖት አባትና መሪ አግኝቶ ማማከር ይችላል፡፡
4. ማንኛውም የህግ ታራሚ ወይም የቀጠሮ ተከሳሽ በሐይማኖት አባትና መሪ የሌላውን የህግ ታራሚና ተከሳሽ የእምነት ነፃነት በማይጋፋ እና በማረሚያ ቤቱ የጥበቃ እና የእርምት ስራ ላይ ተፅዕኖ በማያሳድር ሁኔታ ሐይማኖቱን መከተል ይችላል፡፡

## 39. መረጃ ስለማግኘት መብት

1. ማንኛውም የህግ ታራሚ ወይም የቀጠሮ ተከሳሽ ወደ ማረሚያ ቤት በሚገባበት ጊዜ የማረሚያ ቤቱ የሥነ-ሥርዓት ደንቦች በቃል ወይም በፁሁፍ ይገለፅለታል፣

2. የህግ ታራሚው ወይም የቀጠሮ የተከሳሹ አንብቦ መረዳት የማይችል ከሆነ መረጃው በተሟላ እኳኋን በሚገባው ቋንቋ ወይም ምልክት ይገለፅለታል፡፡

40. አቤቱታ እና ቅሬታ የማቅረብ መብት

1. ማንኛውም የህግ ታራሚ ወይም የቀጠሮ ተከሳሽ በጽሁፍ ወይም በቃል ደረጃዉን ጠብቆ በተቋሙ በተዘጋጀዉ ስርዓት መሠረት አቤቱታ ወይም ቅሬታ የማቅረብ መብት አለው፣
2. የህግ ታራሚው ወይም የቀጠሮ ተከሳሹ የሚያቀርበው አቤቱታ ወይም ቅሬታ በተገቢው ጊዜ ውሳኔ አግኝቶ ውጤቱ ይነገረዋል፣
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 መሠረት በተሰጠ ውሳኔ ላይ አቤቱታ ካለው ለሚመለከተው ኃላፊ ይግባኝ የማቅረብ መብት አለው፡፡

41. ስለ ህግ ታራሚዎች ወይም የቀጠሮ ተከሳሾች ግዴታ

የህግ ታራሚዎች ወይም የቀጠሮ ተከሳሾች ስለ ጥበቃ ሥራ፣ ስለ ሥነ-ሥርዓት አከባበር፣ ስለጽዳት፣ ስለጤና አጠባበቅ፣ ስለማህበራዊ ግንኙነትና ስለሌሎች ጉዳዮች የሚወጡ ደንቦችና መመሪያዎችን የማክበር ግዴታ አለባቸው፡፡

42. ገንዘብ እና ንብረት ስለማስቀመጥ፣

1. ማንኛውም የህግ ታራሚ የሚያገኘው ገንዘብ በስሙ እየተመዘገበ ደረሰኝ ተቆርጦ እየተሰጠው በማረሚያ ቤቱ ወይም ለበለጠ ጥንቃቄ በአጃቢ ፖሊስ ወጥቶ በመረጠው ባንክ ሊቀመጥ ይችላል፤ካስቀመጠው ገንዘብ ላይ እንዲሰጠው ሲጠይቅም በአጃብ ፖሊስ ታጅቦ ሄዶ እንዲወስድ ይደረጋል፤
2. ማንኛውም የህግ ታራሚ በማረሚያ ቤት ወይም ከሌላ ጠያቂ ዘመድ ከሚያገኘው ገንዘብ በኪሱ መያዝ የሚችለው እስከ 500(አምስት መቶ ብር) ብቻ ነው፡፡
3. በማረሚያ ቤቱ ውስጥ በዓይነትም ሆነ በመጠን ለአቀማመጥና ለአያያዝ የማያመች ንብረት ይዞ በመጣ ጊዜ ማረሚያ ቤቱ የታራሚው ወይም የተከሳሹ ቤተሰቦች በግንባር ቀርበው የሚረከቡበትን ሁኔታ ያመቻቻል፡፡

43. ስለ ውክልና

1. ማንኛውም የህግ ታራሚ ወይም ተከሳሽ በማረሚያ ቤት እያለ ውክልና ለመስጠት በጠየቀ ጊዜ ማረሚያ ቤቱ ታራሚዉን ዉክልናን ለመመዝገብ ስልጣን ወደአለዉ አካል በመዉሰድ እንዲወክል ያደርጋል፣

2. በንዑስ አንቀጽ (1) መሰረት ውክልናው የሚሰጠው የህግ ታራሚው ወይም ተከሳሹ ባለበት የማረሚያ ቤት ሆኖ ውክልናው ይህንን እንዲሰራ በተመደበ ሰራተኛ የፊርማ ናሙና እና ሕጋዊ ማህተም ሲረጋገጥ ብቻ ይሆናል፤
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 የተደነገገው ቢኖርም ማረሚያ ቤቱ አስገዳጅ ሁኔታ መኖሩ ሲረጋገጥ ልዩ ውክልና ሊፈቅድ ይችላል፤

44. ስለ ፍቃድ

1. ማንኛውም የህግ ታራሚ በማረሚያ ቤት እያለ ለሚያጋጥመው ማኅበራዊ ችግር ፍቃድ እንዲሰጠው ከጠየቀ ተቋሙ ተገቢነቱን በማረጋገጥ በስራ ሰዓት ብቻ ፍቃድ ሊሰጠው ይችላል፤
2. ማንኛውም የቀጠሮ ተከሳሽ በቀጠሮ ላይ በማረሚያ ቤት እያለ ለሚያጋጥመው ማህበራዊ ችግር ፍቃድ የሚሰጠው በፍርድ ቤት ሲታዘዝ ብቻ ይሆናል፣ ተቋሙ ፍርድ ቤቱ የሚሰጠው ትዕዛዝ ይፈጽማል፣
3. በንዑስ አንቀፅ (1) መሰረት ፍቃድ የሚሰጠው በውክልና ሊከናወኑ በማይችሉ ማህበራዊ ችግሮች ብቻ ይሆናል፣
4. ማንኛውም ፍቃድ የሚሰጠው ማረሚያ ባለበት ከተማ ክልል ውስጥ ብቻ ይሆናል፣ ዝርዝር አፈጻሙ ኮሚሽኑ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል፡፡
5. ማረሚያ ቤቱ ካለበት ከተማ ክልል ውጪ የሚገኙ የህግ ታራሚ ወይም ተከሳሽ የቅርብ ቤተሰቦቻቸው በሞት ሲለዩ በሞት ስለመለየታቸው የሚያስረዳ ማስረጃ በቀረበ ጊዜ እንዲያውቀው ያደርጋል፣

## ክፍል አራት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

45. የዲስፕሊን ቅጣት ዓይነቶች አመዳደብ፣

1) የዲስፕሊን ጉድለት የፈፀመ የህግ ታራሚ ወይም የቀጠሮ ተከሳሽ እንደ ጥፋቱ ክብደት ከሚከተሉት አንዱ ሊወሰንበት ይችላል፡-

ሀ. ምክር

ለ. ለብቻው ወይም በታራሚዎች ወይም በተከሳሾች ፊት የቃል ማስጠንቀቂያ መስጠት፣

ሐ. የፅሁፍ ማስጠንቀቂያ

መ. እስከ አንድ ወር ለሚደርስ ጊዜ የቤት እና ግቢ ውስጥ ፅዳት እንዲያጸዳ ማድረግ፣

ሠ. እስከ እንድ ወር ለሚደርስ ጊዜ በጋራ የመዝናኛ መገልገያዎች እንዳይጠቀም ማድረግ፣

ረ. ከአስራ አምስት ቀን ላልበለጠ ጊዜ ለብቻው ለይቶ ማሰር፣

ሰ. ከአንድ ወር እስከ ስድስት ወር ለሚደርስ ጊዜ በስራ ላይ ተሰማርቶ ከሚያገኘው ገቢ 1/3ኛውን ለመንግስት ገቢ እንዲሆን ማድረግ፣

ሸ. ከሚያገኘው አመክሮ 1/3ኛውን፣ 1/2ኛውን ፣3/4ኛውን እና ሙሉ በሙሉ አመክሮ በመከልከል የሚወሰን ቅጣት ይመደባሉ፡፡

2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ከፊደል ተራ (ሀ) እስከ ፊደል ተራ (መ) የተዘረዘሩት ቀላል የዲስኘሊን ቅጣቶች ሲሆኑ ከፊደል ተራ (ሠ) እስከ ፊደል ተራ (ሸ) የተዘረዘሩት ከባድ የዲስኘሊን ቅጣቶች ተብለው ይመደባሉ፡፡

## 46. ቀላል የዲሲፕሊን ቅጣት የሚያስከትሉ ጥፋቶች

የሚከተሉት ቀላል የዲሲፕሊን ጥፋቶች ናቸው፡-

1. ሌላውን የህግ ታራሚ ወይም ተከሳሽ መሳደብ፣ማንቋሸሽ፣ማዋረድ፣
2. በማንኛውም ሰው ላይ በአጋጣሚ ወይም በድንገት የእጅ እልፊት መፈጸም፣
3. የግል እና የጋራ ንጽህናን አለመጠበቅ፣
4. በግዴለሽነት የዲሲፕሊን ጥፋቶችን መፈጸም፣
5. ቀላል ጥፋትን በመደበቅ ለአጥፊዎች መተባበር፣
6. ትዕዛዝ አለመቀበል፣
7. በፈጸመው ጥፋት በመመሪያዉ መሰረት የተጣለበትን ቅጣት አልፈጽም ማለት፣
8. በባህሪ በምዘና ላይ ተመስርቶ የቀረበለትን የምዘና ውጤት ያለበቂ ምክንያት አልፈርምም ማለት፣
9. ያልተፈቀደ መድሀኒት ማስገባት፣ይዞ መገኘት፣መጠቀም ወይም ሌሎች እንዲጠቀሙ ማድረግ
10. የቆጠራ ሰዓት አለማክበር፣ በቦታው አለመገኘት እና ለመቆጠር ፍቃደኛ አለመሆን
11. በመኝታ ክፍል ወይም በመኖሪያ ቤት ወይም ግቢ ውስጥ ያልተፈቀደ ስራ መስራት፣
12. ሰዎችን ማግለል፣
13. ሕጻን ልጅን አለመንከባከብ፣

14.በትምህርት፣ በስልጠናና በልማት ስራ ላይ ሳይፈቀድለት ማርፈድ፣መቅረት

15.በንግግር ወይም በተግባር ሌሎችን ለፅብ ማነሳሳት፣ መገፋፋት፣ መደገፍ፣ መተባበር፣

16.የተሰጠውን መለያ ዩኒፎርም አለመልበስ፣ በስፌት ቅርጹን መቀየር፣ መጣል፣ መሸጥ እና መለወጥ፣

17.ሴት የህግ ታራሚዎች ወይም ተከሳሾች ወይም ጎብኚዎች ላይ በንግግር፣ በምልክት ወይም በንክኪ ትንኮሳ መፈጸም፣

18.ሊገለገልበት ወይም ለስራ የተሰጠውን የመንግስት ንብረት ላይ ጉዳት ማድረስ፣

19.ያልተፈቀደ የንግድ ስራ መስራት፣

20.የሐሰት ማስረጃ ማቅረብ፣ የሐሰት ምስክርነት መስጠት፣

21.የመስሪያ ቤቱን ወይም የግለሰብን ስም በአሉባልታ ማጥፋት፣

22.ተራ ማጭበርበር እና ማታለል መፈጸም፣ መተባበር ፣ ሌሎችን መገፋፋት ፣

23.ሳያስፈቅድ የልመና ወይም መዋጮ ተግባር መፈጸም፣

24.ሌላውን ታራሚ ወይም ተከሳሽ በከባድ ድምጽ መረበሽ፣

25.ክብደታቸው ከላይ ከተጠቀሱት የጥፋት አይነቶች ተመሳሳይነት ያላቸው የዲሲፒሊን ጥፋቶችን መፈጸም ናቸው፣

26.በልዩ ልዩ የማረም ማነጽ አደረጃጀቶች ላይ አለመሳተፍ

27.ክብደታቸው ከላይ ከተጠቀሱት የጥፋት አይነቶች ተመሳሳይነት ያላቸው የዲሲፒሊን ጥፋቶች፣

**47. ከባድ የዲሲፕሊን ቅጣት የሚያስከትሉ ጥፋቶች**

የሚከተሉት ከባድ የዲስፕሊን ጥፋቶች የወንጀል ተጠያቂነታቸው ሲኖር እንደተጠበቀ ሆኖ በከባድ ዲሲፒሊን የሚጠቃለሉ ናቸው፤

1. በአንቀጽ (46) የተዘረዘሩትን ቀላል የጥፋት ዓይነቶች ከአንድ ጊዜ በላይ መፈጸም፣
2. ሌላውን የህግ ታራሚ ወይም ተከሳሽ መሳደብ፣ማንቋሸሽ፣ማዋረድ፣
3. በማንኛውም ሰው ላይ በአጋጣሚ ወይም በድንገት የእጅ እልፊት መፈጸም፣
4. የግል እና የጋራ ንጽህናን አለመጠበቅ፣
5. በግዴለሽነት የዲሲፒሊን ጥፋቶችን መፈጸም፣
6. ቀላል ጥፋትን በመደበቅ ለአጥፊዎች መተባበር፣
7. ትዕዛዝ አለመቀበል፣

8. በፈጸመው ጥፋት በመመሪያዉ መሰረት የተጣለበትን ቅጣት አልፈጽም ማለት፣
9. በባህሪ በምዘና ላይ ተመስርቶ የቀረበለትን የምዘና ውጤት ያለበቂ ምክንያት አልፈርምም ማለት፣
10. ያልተፈቀደ መድሀኒት ማስገባት፣ይዞ መገኘት፣መጠቀም ወይም ሌሎች እንዲጠቀሙ ማድረግ
11. የቆጠራ ሰዓት አለማክበር፣ በቦታው አለመገኘት እና ለመቆጠር ፍቃደኛ አለመሆን
12. በመኝታ ክፍል ወይም በመኖሪያ ቤት ወይም ግቢ ውስጥ ያልተፈቀደ ስራ መስራት፣
13. ሰዎችን ማግለል፣
14. ሕጻን ልጅን አለመንከባከብ፣
15. በትምህርት፣ በስልጠናና በልማት ስራ ላይ ሳይፈቀድለት ማርፈድ፣መቅረት
16. በንግግር ወይም በተግባር ሌሎችን ለፅብ ማነሳሳት፣ መገፋፋት፣ መደገፍ፣ መተባበር፣
17. የተሰጠውን መለያ ዩኒፎርም አለመልበስ፣ በስፌት ቅርጹን መቀየር፣ መጣል፣ መሸጥ እና መለወጥ፣
18. ሴት የህግ ታራሚዎች ወይም ተከሳሾች ወይም ጎብኚዎች ላይ በንግግር፣ በምልክት ወይም በንክኪ ትንኮሳ መፈጸም፣
19. ሊገለገልበት ወይም ለስራ የተሰጠውን የመንግስት ንብረት ላይ ጉዳት ማድረስ፣
20. ያልተፈቀደ የንግድ ስራ መስራት፣
21. የሐሰት ማስረጃ ማቅረብ፣ የሐሰት ምስክርነት መስጠት፣
22. የመስሪያ ቤቱን ወይም የግለሰብን ስም በአሉባልታ ማጥፋት፣
23. ተራ ማጭበርበር እና ማታለል መፈጸም፣ መተባበር ፣ ሌሎችን መገፋፋት ፣
24. ሳያስፈቅድ የልመና ወይም መዋጮ ተግባር መፈጸም፣
25. ሌላውን የህግ ታራሚ ወይም ተከሳሽ በከባድ ድምጽ መረበሽ፣
26. ክብደታቸው ከላይ ከተጠቀሱት የጥፋት አይነቶች ተመሳሳይነት ያላቸው የዲሲፒሊን ጥፋቶችን መፈጸም ናቸው፣
27. በሰዉና በራስ አካል ላይ ጉዳት መድረስ
28. የማረሚያ ቤቱን ኃላፊዎች ሰራተኞችና የፖሊስ አባሎች መስደብ ዛቻ በንግግር በተግባር ወይም በሌላ አኳኋን ለመልካም ፀባይ ተቀራኒ የሆነ ተግባር መፈፀም
29. ተፈጸመ ከባድ ጥፋት ተመልክቶ አለማሳወቅ ወይም አለመመስከር

## 48. ስለዲስፕሊን ቅጣት አወሳሰን

1) የዲስፕሊን ጥፋት በፈፀሙ የህግ ታራሚዎች ወይም የቀጠሮ ተከሳሾች ላይ ማረሚያ ቤቱ በዚህ ደንብ መሠረት ተገቢውን የዲስፕሊን ቅጣት ሊወሰን ይችላል፣
2) ማንኛውም የዲስፕሊን ቅጣት ከመወሰኑ በፊት የህግ ታራሚው ወይም የቀጠሮ ተከሳሹ ፈጸመ የተባለው ጥፋት ተገልጾለት መልስ እንዲሰጥበት እድል ይሰጠዋል፣
3) የዲስፕሊን እርምጃ ለህግ ታራሚ ወይም የቀጠሮ ለተከሳሽ የሚገለጸው በጽሁፍ ሆኖ የይግባኝ ዕድሉን ጭምር የሚያመለክት መሆን አለበት፣
4) በህግ ታራሚዎች ወይም በቀጠሮ በተከሳሾች ላይ የሚወሠነው የዲስፕሊን ቅጣት የይርጋ ጊዜ በሚወጣው መመሪያ ይወሠናል፡፡

## 49. በማግለያ ውስጥ የህግ ታራሚን ወይም ተከሳሽን መያዝ

1) የህግ ታራሚው ወይም የቀጠሮ ተከሳሹ በሚያሳየው የባህሪ አደገኛነት በራሱ፣ በጥበቃ አባላት እና በሌሎች የህግ ታራሚዎች ወይም ተከሳሾች ላይ ጉዳት ሲያደርስ አደገኝነቱን ለማስቆም ወይም ስጋቱን ለመቀነስ በሚያስችል ሁኔታ የአካሉን እንቅስቃሴ በሚገድብ በካቴና አደጋውን ለመከላከል በሚያስችል ጊዜ ውስጥ በማረሚያ ቤቱ ኃላፊ ዕውቅና በማያሰቃይ መልኩ ብቻ ለይቶ ማስቀመጥ ይችላል፡፡
    2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተደነገገው የቀጠሮ ተከሳሾች እና የህግ ታራሚዎች በፍርድ ቤትና አስተዳደራዊ ጉዳዮች ለሚወሰድ የጥንቃቄ አያያዝ የሚመለከት አይደለም፤
    3) በማግለያ ቤት ውስጥ ለብቻ ለይቶ ማስቀመጥ እንደ መጨረሻ አማራጭና በተቻለ መጠን ለአጭር ጊዜና በሚመለከተው ኃላፊ ሲፈቀድ ብቻ ሊፈጸም ይገባል፤
    4) የአዕምሮ ሕሙማን ወይም አካል ጉዳተኛ የሆነ ተከሳሽ ወይም የህግ ታራሚ በማግለያ ቤት ማቆየት ሁኔታቸውን የሚያከብድ መሆነን በሐኪም ሲረጋገጥ አይፈጸምም
    5) ሕጻናት ያላቸው ሴቶች እና መጫተች በማግለያ ቤት ውስጥ በማናቸውም ጊዜ ውስጥ እንዲቆዩ አይደረግም፡፡

## 50. በህግ ታራሚ ወይም በቀጠሮ ተከሳሽ ስለሚፈፀም ወንጀል

ማንኛውም የህግ ታራሚ ወይም የቀጠሮ እስረኛ በማረሚያ ወይም በማረፊያ ቤት ቆይታው የወንጀል ድርጊት ቢፈጽም በወንጀል ሕግ መሠረት ተጠያቂ ይሆናል፡፡

## 51. ከማረሚያ ቤት ያመለጡ የህግ ታራሚዎች ወይም የቀጠሮ ተከሳሾች ላይ ስለሚወሰድ እርምጃ

1) ከማረሚያ ወይም ከማረፊያ ቤት አምልጦ የተያዘ ወይም ሙከራ ያደረገ ወይም ለማምለጥ የተሰናዳ ታራሚ ወይም ተከሳሽ በፈጸመው ወንጀል ክስ ይመሰረትበታል፤

2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት የሚወሰድ እርምጃ ታራሚው ከነበረበት ሥራ መደብ ዝቅ ወዳለ የሥራ ደረጃ መመደብ ወይም ከዝቅተኛ ጥበቃ ማረሚያ ቤት ወደ መካካለኛ ወይም ከፍተኛ ጥበቃ እንዲዘዋወር ይደረጋል፡፡ መረጃውም ተመዝግቦ ይያዛል፣

3) የህግ ታራሚው ከማረሚያ ቤት አምልጦ ውጭ የቆየበት ጊዜ ሲፈጽም ከነበረው ቅጣት ላይ ቅናሽ አይደረግለትም፡

## 52. በህግ ታራሚዎች ላይ ስለሚጣሉ ቅጣቶች አፈጻጸም

ማንኛውም የህግ ታራሚ ፍርድ በመፈፀም ላይ እያለ በሌላ የወንጀል ጥፋት ምክንያት የፍርድ ውሳኔ ከተላለፈበት የተወሰነበትን ተጨማሪ ፍርድ የሚፈፀመው የመጀመሪያው የፍርድ ውሳኔ ከተፈፀመ በኋላ ነው፤ .

## 53. የእስር መሣሪያዎች አጠቃቀም፤

መሣሪያዎች በሚከተሉት ሁኔታዎች በተከሣሾችና በታራዎች ላይ ተግባራዊ ይሆናሉ፤

ሀ. የህግ ታራሚው ወይም የቀጠሮ ተከሣሹ አደገኛ ባህሪ እራሱን፣ የማረሚያ ፖሊሰ ወይም በሌሎች እስረኞች ላይ አደጋ የሚያደርስ ሲሆን

ለ. የህግ ታራሚው ወይም የቀጠሮ ተከሣሹ በፍርድ ቤት ወይም በአስተዳደር በእጀባ ወቅት እንዳያመልጡ፤

ሐ. የእስር መሣሪያዎች መተግበር ያለባቸው እንቅስቃሴ የሚስከትሉትን አደጋዎች ለመቅረፍ ይህም ያነሰ የቁጥጥር ዘዴ ውጤታማ በማይሆንበት ጊዜ

መ.የእገዳው ዘዴ የህግ ታራሚውን እንቅስቃሴ ለመቆጣጠር በሚያስችለው ደረጃ እና በተፈጠሩት አደጋዎች ተፈጥሮ ላይ በመመርኮዝ አነስተኛ ጣልቃ ገብነት ያለው ዘዴ አስፈላጊ እና ምክንያታዊ መሆን አለበት

ሠ. የእስር መሣሪያዎች የሚፈለገውን ጊዜ ብቻ እና ያልተገደበ እንቅስቃሴ የሚያሰከትለው ስጋቶች እስከሚቀሩበት ጊዜ ውስጥ ብቻ ይፈፀማሉ

ረ. በሴቶች ላይ የማገጃ መሣሪያዎች ከወሊድ በፊት በወሊድ ጊዜ እና በኋላ መጠቀም አይቻልም፡፡

## 54. የህግ ታራሚዎችና ተከሣሾችና መኖሪያ አካባቢዎች ፍተሻ

1. የማረሚያ ቤቱን ደኅንነት ለማስጠበቅ የሚደረገው ፍተሻ የህግ ታራሚዎች ወይም ተከሳሾች ወይም በተከሰሱ ሰዎች ሰብዓዊ ክብርና ግላዊነቱን መከበሩን ባረጋገጠ መንገድ መሆን አለበት፤
2. ማረሚያ ቤቱ ያከናወናቸውን ፍተሻ በመዝገብ ተለይቶ መረጃው መያዝ እና በተለይም የአካል ፍተሻዎች የተከናወኑበት ምክንያት፣ ፍተሻውን ያከናወኑ ሰዎች ማንነትና በፍተሻው የተገኘው ውጤት ተመዝግቦ ለሚመለከተዉ አካል መተላለፍ አለበት፤
3. የድንገተኛ ፍተሻ ሆኖ የአካልና የውስጥ ሰውነት ፍተሻዎች በተመረጡ የማረሚያ ፖሊስ አባላት ሆኖ በሚስጥራዊ፣ በባለሙያና፤ በተመሣሣይ ፆታ መደረግ አለበት፤ ይህ ፍተሻው ዓይነት አስፈላጊና ምክናታዊ መሆኑ መረጋገጥ አለበት
4. የውስጥ ሰውነት ፍተሻ በጤና አጠባበቅ ሰራተኛ ወይም በሌለበት ጊዜ ይህንን እንዲያከናውኑ በንፅህና እና ጤና ደኅንነት ደረጃ በሰለጠኑ ሰዎች ይከናወናል፤
5. የህግ ታራሚዎች ከፍርድ ቤት ሕጋዊ ጉዳዮቻቸውን ጋር የተያያዙ ሰነዶች የማረሚያ ቤቱ አስተዳደር ጠይቀው ማግኘት ሳይጠብቅ በግላቸው መያዝ ይችላሉ

## 55.ስለ ፍርድ ውሳኔ መጀመሪያና መጨረሻ ጊዜ

1) የፍርድ ውሳኔ ጊዜ የሚጀመረውና የሚፈፀመው ውሳኔውን በሰጠው ፍርድ ቤት ትዕዛዝ መሠረት ይሆናል፣
2) የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ድንጋጌ ቢኖርም ታራሚው በአመክሮ፣ በይቅርታ ወይም በምህረት ከእሥር ሊፈታ ይችላል፡፡

## 56. ማረሚያ ቤቱ ግዴታ

1) የህግ ታራሚዎችና የቀጠሮ ተከሳሾችን ሰብዓዊ መብት ማክበርና ማስከበር፣ መሠረታዊ ፍላጎቶቻቸውን ማሟላትና ተገቢውን የተሐድሶና እርምት አገልግሎቶችን እንዲያገኙ ማድረግ
2) የህግ ታራሚዎችና ተከሳሾችን በቀጠሮ ቀናቸው ፍርድ ቤት ማቅረብና ሌሎች በፍርድ ቤት የሚሰጡ ትዕዛዞችን መፈጸምና የፍትህ ጉዳዮችን ማስፈጸም፤
3) የህግ ታራሚዎች የፍርድ ጊዜያቸውን ሲፈጽሙ መፈታት እንዲችሉ የሚመለከታቸው ኃላፊዎች ወይም ሰራተኞች የግል ማህደሮቻቸውን በየጊዜው መመርመር፤

4) የህግ ታራሚዎችና የቀጠሮ ተከሳሾችን ማህደር የአስተዳደር ሥርዓቶች በማደራጀት በማስረጃ ላይ የተመሰረተ ውሳኔ ለመስጠት እና በአንድ ክፍል የሚታሰሩ ህግ ታራሚዎች ብዛትን ጨምሮ ከእስር ቤት ማህበረሰብ ባህሪያት ጋር ተያያዥነት ያላቸው መረጃዎችን በማደራጀት ጥቅም ላይ የማዋል፤
5) ማንኛውም የህግ ታራሚ የፍርድ ጊዜውን ሲጨርስ ወይም ይቅርታ ወይም ምህረት ሲያገኝ ወይም በአመክሮ እንዲፈታ ሲወሰን ማረሚያ ቤቱ ታራሚውን በዕለቱ መፍታት፣
6) ማንኛውም ተከሳሽ በቀጠሮ ላይ እያለ በሕግ አግባብ ባለው ፍርድ ቤት ትዕዛዝ እንዲፈታ ሲወሰን በዕለቱ መፍታት፣
7) ቀጠሮ ቤት ጉዳዩን ሲከታተል የቆየ ተከሳሽ ፍርድ ሲያገኝ ወደ ሚመለከተው ማረሚያ ቤት/ክፍል/ ማዛወር፣
8) ለተከሳሾች ፍርድ ቤት የሚሰጣቸው ቀጠሮ ቀን በመከታተል መዝግቦ እንዲያዝ ማድረግ፤
9) ለሴቶች፣ ለሕጻናት፣ ለአካል ጉዳተኞች በዕድሜ ለገፉና በማይድን በሽታ ለተያዙ እስረኞች ልዩ ድጋፍና እንክብካቤ ማድረግ፤
10) ማንኛውም ማረሚያ ወይም ማረፊያ ቤት የህግ ታራሚው የሞት ቅጣት ወይም የዕድሜ ልክ ፍርደኛ ከሆነ የይግባኝ ጊዜው ሳይጠናቀቅ ነጻ የሕግ ድጋፍ እንዲያገኝ የማመቻቸት ግዴታ አለበት፤
11) የህግ ታራሚዎች አያያዝ ለማሻሻልና ለማሳደግ የሚያግዙ የውስጥ ወይም የውጭ አካላት ቁጥጥርና ክትትል ድጋፍ ማድረግ ፣
12) በዚህ ደንብ መሠረት የሚታዩ ጉድለቶች መኖራቸውን ሲያረጋግጥ ወዲያውኑ ማስተካከል ወይም ከአቅም በላይ ሲሆን ለሚመለከተው አካል ወዲያውኑ የማሳወቅ ግዴታዎች አሉበት፡፡

## 57. ስለ ህግ ታራሚዎችና የቀጠሮ እስረኞች ግዴታዎች

የህግ ታራሚዎች እና የቀጠሮ ተከሳሾች ይህን ደንብ ተከትለው በሚወጡ መመሪያዎችና ስታንዳርዶች የተጣሉባቸው ግዴታዎች እንደተጠበቁ ሆነው የሚከተሉት ግዴታዎች ይኖርባቸዋል፡-

1) በእጀባ ወቅት በእጅ ካቴና እንዲታሰር ሲታዘዝ ተቀብሎ የመፈጸም፤
2) በማረሚያ ቤቱ የፖሊስ አባሎች እና የሥራ ኃላፊዎች የሚሰጠውን ሕጋዊ ትዕዛዝ መቀበልና መፈጸም፤

3) በማረሚያ ቤት ውስጥ የወንጀል ተግባር ሲመለከት የማሳወቅ፤ የምስክርነት ወይም የከሳሽነት ቃል የመስጠት፤

4) የማረሚያ ቤቱን ወደ መኖሪያ ቤት መግቢያ የቆጠራ ሰዓት የማክበር፤

5) የህግ ታራሚዎች ወደ ማደሪያ ክፍሎቻቸዉ እንደ አየሩ ሁኔታ ታይቶ ከቀኑ 12፡00 ሰዓት ገብተዉ በሩ መዘጋት አለበት፡፡

6) የዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀጽ 5 ድንጋጌ ቢኖርም በተፈጥሮና በሰዉ ሠራሽ አደጋ ጊዜ ስያገጥም ማለትም ከባድ ዝናብ አዉሎንፋስ የተቀላቀለ ሲሆን አየሩ በጉም ሲሸፈንና ሲጨልም፤ በጊቢ ዉስጥ ሁከት ሲፈጠርና የመሳሰሉት ችግሮች ሲፈጠሩ ወደማደሪያ ክፍላቸዉ መግባት ይኖርባቸዋል፡፡

7) በማረሚያ ቤቱ የታራሚዎች መኖሪያ ግቢ ዉስጥ የእሳት አደጋ ሲከሰት፤ታራሚዎች በቤት ዉስጥ ከሆኑ ለበለጠችግር ይጋለጣሉ ተብሎ በተቋሙ ኃላፊና የዕለቱ ተረኛ ሀላፊ ሲታመንበት በሩ ተከፍቶላቸዉ በተዘጋጀላቸዉ ቦታ ላይ እንዲቆዩ ይደረጋል፡፡

8) የሌሎች የህግ ታራሚዎና የቀጠሮ ተከሳሾች ሰብአዊ መብት እና ክብር ጠብቆ፣ ሰላምና ደህንነት አክብሮ የመኖር፤

9) መንግሥት እንዲገለገልበት የሚሰጠውን ማንኛውንም ንብረት በአግባቡ መጠበቅ እና ሲወጣ የማስረከብ፤

10) በማረም ማነፅ ባለሙያዎች የሚሰጠውን የምክር፣ የማህበራዊ፣ የንቃተ ሕግና ሥነ-ምግባር ግንባታና ባህሪ ቀረጻ የመከታታልና የትምህርትና ስልጠናና የልማት ሥራ ማቋቋም ተግባራት ላይ መሣተፍ፤

11) የሚሰጠውን ዩኒፎርም ማረሚያ ቤቱ በሚያወጣው መመሪያ መሠረት መልበስ እና ፅዳቱን ጠብቆ የመጠቀም፤

12) ሌሎች ለማህበራዊ ግንኙነት አስፈላጊ የሆኑ ኃላፊነቶችን የመወጣት

## 58. የተከለከሉ ተግባራት

በወንጀል ሕጉና በሌሎች ሕጎች የተደነገጉ ክልከላዎች እንደተጠበቀ ሆነው የህግ ታራሚዎች የቀጠሮ እስረኞችን በማረሚያና ማረፊያ ቤት ቆይታቸው የሚከተሉትን ተግባራት መፈፀም አይችሉም፡-

1) የማረሚያ ቤቱን ማህበረሰብ ሰላም እና ደህንነት በሚያውክ አድማ፣ ብጥብጥ እና ማንኛውም መሰል ተግባርን ማነሳሳት፣ መሳተፍ እና መርዳት፤

2) የቡድን ፀብን ማነሳሳት፣ መሳተፍ እና መርዳት፤
3) ሌሎች የህግ ታራሚዎችና የቀጠሮ እስረኞችን ወይም የማረሚያ ቤቱ ሠራተኞችን የመሳደብ፣ የማዋረድ እና የማሸማቀቅ ተግባርን በንግግር፣ በጽሑፍ ወይም በምልክት መፈፀም፤
4) ኮሚሽኑ በሚያወጣው መመሪያ መሠረት ወደ ማረሚያ ቤት እንዳይገቡ የተከለከሉ ነገሮችን ለማስገባት መሞከር፣ ማስገባት፣ ይዞ መገኘት ወይም መጠቀም፡አይቻልም ፡፡

59. ስለ እስራት ጊዜ ቅናሽ

1) የህግ ታራሚው ወደ ማረሚያ ቤት ሲገባ በወንጀል ሕጉ ድንጋጌ መሠረት በአመክሮ እና በይቅርታ የእስራት ቅናሽ ሊያገኝ የሚችልበት ሁኔታ ይገለጽለታል፣
2) የህግ ታራሚው የእሥራት ቅናሽ ተደርጎለት እንደሆነ ቅናሹ የሚደረገው በጠቅላላው ከተፈረደበት የእሥራት ጊዜ ላይ ይሆናል፣
3) የህግ ታራሚው በገንዘብና በእሥራት እንዲቀጣ ሲፈረድበት ወይም ገንዘቡን መክፈል ባለመቻሉ ቅጣት ሲፈረድበት ቅናሽ የሚደረገው በማረሚያ ቤት እንዲፈጸም ከታዘዘው የእስራት ቅጣት ላይ ብቻ ነው ፣
4) በማንኛውም የሕክምና ተቋም ገብቶ በመታከም ላይ የሚገኝ የህግ ታራሚ በማረሚያ ቤት እንዳለ ይቆጠራል፡፡ሆኖም የህግ ታራሚው ሆን ብሎ ሕመሙን በራሱ ላይ እንዲደርስ በማድረግ ወይም በማታለል ሆስፒታል ተኝቶ እንደሆነ በዚህ አኳኋን ሆስፒታል ተኝቶ ያሣለፈው ጊዜ ሊፈፀመው ከሚገባው የእስራት ቅጣት ጋር አይታሰብለትም፣
5) በማንኛውም ምክንያት የእሥራት ቅናሽ እንዲያገኝ በሚደረግበት ጊዜ ኮሚሽኑ ለህግ ታራሚው የተቀነሰለትን ቅነሳ እንዲያውቀው መደረግ አለበት፣
6) በህግ ታራሚው ላይ የተጣለበት ቅጣት፣ የተፈቀደለት ወይም የተከለከለው የእሥራት ቅናሽ እና እሥራቱ የሚያልቅበት ጊዜ ተመዝግቦ ይያዛል፤
7) በእስራትና በገንዘብ የተቀጣ የህግ ታራሚ ገንዘቡን መክፈል ካልቻለ የእስራት ቅጣቱን አመክሮ ታስቦለት ከመጨረሱ በፊት ውሣኔ ለሰጠው ፍርድ ቤት በማሣወቅ ፍርድ ቤቱ የሚሠጠውን ተለዋጭ ትዕዛዝ ማረሚያ ቤቱ ያስፈፅማል፣

8) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (7) ያለው ድንጋጌ መሠረት ፍርድ ቤቱ በቀረበለት ጉዳይ ተለዋጭ ትዕዛዝ ካልሰጠና የህግ ታራሚው የእስራት ጊዜውን ያለአመክሮ ከጨረሰ እንዲፈታ ይደረጋል፡፡

## 60 የአመክሮ እና ይቅርታ ኮሚቴ ስለማቋቋም

1. በአመክሮ ወይም በይቅርታ የሚፈቱ የህግ ታራሚዎች ጉዳይ የሚያጠና አንድ ሰብሳቢ እና አምስት አባላት ያሉት ኮሚቴ ይቋቋማል ፡፡
2. ኮሚቴው የሚያቀርበው የውሳኔ ሀሳብ ለማረሚያ ቤቱ ማናጅመንት ቀርቦ በሃላፊ ፀድቆ ለመጨረሻ ውሳኔ አግባብ ላለው አካል ይቀርባል፡፡

## 61. ስለ አመክሮ አሰጣጥ

1) ማንኛውም የህግ ታራሚ አመክሮ የሚያገኘው፡-

ሀ. በማረሚያ ቤት መልካም ጠባይ ካሳየ፣የማረሚያ ቤቱን ደንብ የሚያከብርና በቀይታዉም የታነፀ ስለመሆኑ ማረሚያ ቤቱ ማረጋገጫ ከሰጠ

ለ. ከተፈታ በኋላ መልካም ውጤት ሊያስገኝ ይችላል ተብሎ ከተገመተ፣

ሐ. በፍርድ ቤት ውሣኔ መሠረት የሚፈለግበትን ማንኛውም ክፍያ አጠናቅቆ የፈጸመ ወይም በወንጀል ሕጉ መሠረት ተለዋጭ ትዕዛዝ ሲሰጥበት፣

መ. ሁለት ሦስተኛውን የእሥራት ቅጣት ከፈጸመ ወይም የእድሜ ልክ እሥራት ተፈርዶበት ሃያ አመት ከታሠረ፣

ሠ. ለማሕበራዊ ኑሮ መልካም ዝንባሌ ማሳየቱ፣ መታረሙና የባህሪ ለውጥ ማምጣቱ በማረሚያ ቤቱ የባህሪ ምዘና ሲረጋገጥ፣

ረ. ደጋጋሚ ወንጀለኛ ያልሆነ ፣

ሸ. ለደረሰው ጉዳት በፍርድ ቤት በተወሠነ መሠረት ወይም ከተበዳዩ ጋር በተደረገው የእርቅ ስምምነት መሠረት ካሣ የከፈለ ወይም የእርቅ ጥያቄው ተቀባይነት ካላገኘ ይህንኑ የሚያስረዳ ሠነድ ያቀረበ ወይም ዕርቅ ለመፈጸም ስለመሞከሩ ሕጋዊ ማስረጃ ያቀረበ፣

ቀ. በዲሲፒሊን ጥፋት ምክንያት በከፊል ወይም ሙሉ በሙሉ አመክሮ እንዳያገኝ ቅጣት ተላልፎበት በይርጋ ውድቅ የሆነ፣ ዝርዝር አፈጻጸሙ በመመሪያ ይወሰናል፣

በ. የህግ ታራሚው የአመክሮ ቅናሽ ተደርጐለት ሲፈታ ኮሚሽኑ የሚሠጠውን የቅድመ ሁኔታ ግዴታ ተስማምቶ የፈረመ መሆን ይኖርበታል፡፡

2) በተደራራቢ ወንጀሎች ፍርድ የተወሰነበት የህግ ታራሚ ባሳየው የባህሪ መለወጥ ላይ ተመስርቶ በእያንዳንዱ ወንጀል ከተሰጠው ፍርድ በቅደም ተከተል አመክሮ እንዲያገኝ ይደረጋል

3) ለአመክሮ ግዴታ የሚቀመጠው ጊዜ በወንጀል ሕጉ በተደነገገው መሠረት ይሆናል፡፡ ይህን ጊዜ ሳይፈፅም በሌላ ወንጀል ተከሶና ተፈርዶበት ወደ ማረሚያ ቤት ሲገባ ተቋሙ ለፍርድ ቤት በማሳወቅ በሚሰጠው ውሳኔ መሠረት በአመክሮ ቅናሽ የሰጠውን ጊዜ በማንሣት ቅጣቱን እንዲፈፅም ያደርጋል፣

4) በልዩ ልዩ ምክንያት አመክሮ እንዳያገኝ የተወሰነበት የህግ ታራሚ ከኮሚሽኑ ወደ ክልል ማረሚያ ቤቶች እንዲዛወር ሲደረግ ለተዛወረበት ማረሚያ ቤት ይህንኑ እንዲያስፈጽም ያሳውቃል፡፡

5) አመክሮ ክልከላ የተደረገበት የህግ ታራሚ ክልከላው በሚያበቃበት ጊዜ እንደገና ለአመክሮ መቅረብ ይችላል፤ ዝርዝሩ በመመሪያ ይወሰናል

## 62. ይቅርታ ስለሚጠየቅላቸው የህግ ታራሚዎች

1) ይቅርታ የሚጠየቅላቸው የህግ ታራሚዎች በይቅርታ ስነሥርዓት አዋጅ ቁጥር 134/2008 መሠረት የይቅርታ አፈፃፀሙ ይከናወናል፡፡

2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 እንደተጠበቀ ሆኖ በማይድን በሽታ የተያዙ፣ በዕድሜ ለገፉ፣ በማረሚያ ቤት ቆይታቸው መልካም ባህሪ ላሳዩ የህግ ታራሚዎች የሕዝብና መንግስት ጥቅም ለማስጠበቅ ሲባል በማረሚያ ቤቱ አነሳሽነት ይቅርታ ሊጠየቅላቸው ይችላል፤ አፈጻጸሙ በመመሪያ ይወሠናል፣

## 63. የህግ ታራሚዎች ከእሥር ሲፈቱ ሊሟሉ ስለሚገባቸው ሁኔታዎች፣

1) ማንኛውም የህግ ታራሚ በአመክሮ፣ በይቅርታ በምህረት ወይም የእሥራት ጊዜውን ጨርሶ ወይም ማንኛውም ተከሳሽ በሕግ አግባብ ባለው ፍርድ ቤት ትዕዛዝ ከእሥር ሲፈታ በማረሚያ ወይም በማረፊያ ቤት ያስቀመጠውን ገንዘብ፣ ልብስ ወይም ዕቃ ካለ ደረሰኝ ፈርሞ ይወስዳል ወይም ለሚወክለው ሰው ወይም ድርጅት ይሰጥለታል፣

2) የህግ ታራሚው ሲፈታ ገንዘብ የሌለው መሆኑ ከተጣራ በኋላ ወደ ቀድሞ መኖሪያ ቦታው ለመመለስ የሚያስችለው ለመጓጓዣና ለስንቅ የሚሆን ገንዘብ ማረሚያ ቤቱ ይሰጠዋል፣

3) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) ያለው ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ በደንብ መተላለፍ ውጪ ያሉ የውጭ ዜጋ የህግ ታራሚ ኮሚሽኑ ለሚመለከተዉ አካል ታራሚዉን እንዲረከበረ በደብዳቤ ያሳዉቃል ፤

4) ማንኛውም የህግ ታራሚ ከእሥር ሲፈታ ማረሚያ ወይም ማረፊያ ቤቱ ከእሥር የተፈታ መሆኑን የሚያረጋግጥ የምስክር ወረቀት ይሰጠዋል፡፡

## ክፍል አምስት
## ልዩ ልዩ ድንጋጌ

### 64. የውስጥ ገቢን ስለማስተዳደር

1) ኮሚሽኑ በስሩ ከሚያስተዳድራቸው ከግብርና፣ከእንጨትና ከብረታብረት የስልጠና ውጤቶች፣ ከአነስተኛ ኢንዱስትሪና ልዩ ልዩ ከውስጥ ገቢ ምንጮች የተገኙ ሐብቶች በመንግስት ፋይናንስ ደንብ መሠረት ይቆጣጠራል፤ ለአስፈላጊው አላማ ያውላል

2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ድንጋጌ መሠረት የሚከናወኑ የፋይናንስ ወጪዎች ብክነት እንዳይኖር አስፈላጊው የሕግና የአሰራር ማዕቀፍ እንዲዘረጋ ይደረጋል

3) ኮሚሽኑ በልዩ ልዩ ማዕከላት ስር የሚገኙ መዝናኛ ክበባትና እና የህብረት ሱቅ የአገልግሎት በዚህ ደንብ እንዲቋቋሙ ተደርጓል

4) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 መሠረት የተቋቋሙ የሻይ ቡና መዝናኛ ክበባትና የአገልግሎት ሱቆች የሚመነጩ ትርፎች ለህግ ታራሚው ወቅታዊ እና ዘለቄታዊ የማህበራዊ ችግር መፍቻ እንዲውል ይደረጋል ዝርዝሩ በመመሪያ ይወሰናል፤

### 65. የአዕምሮ ውጤት ጥበቃ መብት ሰለመረጋገጡ

ማንኛውም የህግ ታራሚ በማረሚያ ቤቱ ቆይታ ጊዜ ውስጥ የአዕምሮ ውጤት በሆኑ የፈጠራ ሥራዎች ላይ ሕጋዊ መብት እንዲጠበቅለት ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በጋራ ይሰራል፤

### 66. የማረም ማነጽ ጥናትና ምርምር

ኮሚሽኑ በሕግ የተሰጠውን የማረም ማነጽ ተልዕኮ ውጤት በራሱ ወይም በሌላ ሦስተኛ ወገን ጥናትና ምርምር ያደርጋል በግኝቱ መሠረት ሥራውን ያከናውናል

### 67. የውጭ ቁጥጥር ሥርዓት

1) የህግ ታራሚዎችን መብት አከባበር እና አያያዝ ለማሻሻል በሕግ ስልጣን የተሰጣቸው አካላት በኮሚሽኑ የሚገኙ ማናቸውም ቅርንጫፎችን ያለቅድመ-ማስጠንቀቂያ የመጎብኘት እና ቅሬታ ያላቸውን በነፃና ሚስጥሩን በጠበቀ መንገድ እንዲያነጋግሩ ይደረጋል፤

2) የሰብዓዊ መብት አያያዝ ለማሻሻል የተቋቋሙ የሲቪል ማህበራት፣ የምርምር ተቋማትና ተመራማሪዎች ኮሚሽኑን በማስፈቀድ የመጡበትን ተግባር ሊፈጽሙ ይችላሉ፡፡

3) ኢትዮጵያ አባል በሆነችባቸው ወይም ባጸደቀቻቸው ዓለም አቀፍ ስምምነቶች መሠረት የተቋቋሙ ኮሚሽኖች፣ ኮሚቴዎች፣ ሪፖርተሮችና የመሳሰሉት በፍትህ ቢሮ ሲፈቀድ ጉብኝት ማድረግ ይችላሉ፤

68. **መገናኛ ብዙሐን**

1) የማረምና ማነጽ ተግባርና የህግ ታራሚዎች ደህንነት ጥበቃ ሥራ በማያስተጓጉል ሁኔታ የመንግስት የመገናኛ ብዙሃን በማረሚያና ማረፊያ ቤቶች ውስጥ ጉብኝት ማድረግ ይችላሉ፡፡

2) የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ያለው ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ የመንግስት የመገናኛ ብዙሐን ተነጻጻሪ የሕዝብና የግለሰብ ጥቅሞች ለማስጠበቅ የወጡ ተገቢ ገደቦች በመተላለፍ የሚሰራጩ ህትመቶችና ብሮድካስት ዘገባዎች አግባብነት ባለው ሕጎች መሠረት ተጠያቂ ይደረጋሉ፡፡

69. **የህግ ታራሚዎችና የተከሳሾች የባህር መዝገብ ስለማደራጀት**

1. የህግ ታራሚዎችና የቀጠሮ ተከሳሾች በወንጀል ዓይነት፣ የፍርድ ልክና ሙሉ የሕይወት ታሪክ የሚመዘገብበት የባህር መዝገብ ይደራጃል፣

2. የህግ ታራሚዎች መረጃ በዘመናዊ ቴክኖጂ የመረጃ አያያዝ ሥርዓት ይደራጃል፡፡

3. የመዝገብ ደህንነቱ የተጠበቀ የኦዲት መንገድ ለማረጋጋጥ እና በመረጃ ቋት ውስጥ ያለ ማንኛውም መረጃ አላግባብ የማግኘት ወይም የማሻሻል ሒደት መከላከል የሚያስችል ይደረጋል፡፡

4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ስር የተደነገገው መረጃ በሚስጥራዊነት እንዲያዝ የሚደረግና በስራቸው ምክያንያት መረጃው እንዲያውቁ ከሚደረጉ ውጭ ለማንኛውም ሰው የተከለከል ነው

70. **የዕርቅ አሰራር ተፈጻሚነት**

በወንጀል ጉዳይ በሕግ ዕርቅ እንዲፈጸምባቸው በተደነገጉ ጉዳዮች ላይ ተቋሙ የህግ ታራሚዎችን ወደ ሕብረተሰብ መልሶ የመቀላቀል ተልዕኮ ለማሣካት ሁኔታዎች ያመቻቻል፤

**71. መመሪያ ስለማውጣት**

ኮሚሽኑ ይህን ደንብ ለማስፈጸም አስፈላጊ የሆኑትን መመሪያ ሊያወጣ ይችላል፡፡

**72. ተፈፃሚነት ስለማይኖራቸው ደንቦችና መመሪያዎች**

1) የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 68/2005 በዚህ ደንብ ተሽሯል፡፡

2) ከዚህ ደንብ ጋር የሚቃረን ማናቸውም ደንብ ወይም መመሪያ በዚህ ደንብ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖረውም፡፡

**73. ደንቡን የሚያጸናበት ጊዜ**

ይህ ደንብ በክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት ከጸደቀበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል፤

አሶሳ………/……ቀን 2017 ዓ.ም

አሻደሊ ሀሰን አልአጀብ

የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግስት

ርዕሰ መስተዳድር

.